# በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

# የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

# የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች

# የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ማንዋል

# (የጸደቀ)

ጥር/2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 3
1. መግቢያ ........ 3
1.1. የቃላት ትርጓሜ ........ 4
1.2. የማንዋሉ ህጋዊ መሰረት ........ 7
1.3. የማንዋሉ ዓላማ ........ 7
1.4. የማንዋሉ አስፈላጊነት ........ 7
1.5. የማንዋሉ መርሆዎች ........ 8
1.6. የተፈፃሚነት ወሰን ........ 8
1.7. የማኑዋሉ ተጠቃሚዎች ........ 8
1.8 የሚጠበቅ ውጤት ........ 9
ክፍል ሁለት ........ 10
2. የምሰሶዎች እና የተግባራት ትስስር ማዕቀፍ/Framework/ ........ 10
2.1. የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ምሰሶዎች ........ 10
2.1.1. የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ምሰሶዎች እና ዋና ዋና ተግባራት ........ 10
2.1.1.1. ምቹ አከባቢን መፍጠር /Enabling Environment ........ 16
2.1.1.2. የቴክኖሎጆ ልማት እና ሽግግር እና ፈጠራ ........ 17
2.1.1.3. መሠረተ ልማት ........ 18
2.1.1.4. የገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነት ........ 19
2.1.1.5. ግብዓት አቅርቦት ........ 20
2.1.1.6. እውቀት እና ክህሎት ........ 21
2.1.1.7. የፋይናንስ አቅርቦት ........ 23
2.1.1.8. የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ........ 24
2.2. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ስልቶች ........ 25
2.2.1. ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት ........ 25
2.2.2. ክላስተር መሰረት ያደረገ ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ........ 26
2.2.3. የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር፣ ........ 27
2.2.4. ዲጅታላይዜሽን ........ 28
2.2.5. ኢንተርፕራይዝ ተኮር ኤክስቴሽን አገልገሎት ........ 28

2.3. የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የአፈጻጸም ቅደም ተከተል ..... 28
ክፍል ሶስት ..... 31
3. የአስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ..... 31
3.1 የአስፈፃሚና ፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ..... 31
3.1.1. ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ..... 31
3.1.2. የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ..... 31
3.1.3. የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ..... 32
3.1.4. የክልልና ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ባለድርሻ አካለት ተግባርና ኃላፊነት ..... 33
3.2. የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ..... 34
3.2.1. የግብርና ሚኒስቴር ..... 34
3.2.2. የማዕድን ሚኒስቴር ..... 35
3.2.3. የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ..... 35
3.2.4. የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ..... 36
3.2.5. የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ..... 36
3.2.6. የትምህርት ሚኒስቴር ..... 37
3.2.7. የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ..... 37
3.2.8. የኢትዮጵ ኢንዱስትሪ ግብአት ልማት ድርጅት ..... 37
3.2.9. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ..... 38
3.2.10. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ..... 39
3.2.11. ባንኮች፣ የብድርና ቁጠባ ተቋማትና የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አ/ማህበራት ..... 40
ክፍል አራት ..... 42
4. የተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ ..... 42
4.1. የተጠቀሚዎች መብት ..... 42
4.2. በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከተጠቃሚዎች የሚጠበቁ ግዴታዎች ..... 42
ክፍል አምስት ..... 44
5. መረጃ፣ ክትትል፣ ድጋፍና ግብረ መልስ ..... 44
5.1. መረጃ አያያዝ ..... 44
5.2. ክትትል፣ ድጋፍ እና ግብረ መልስ ..... 44
5.3. የአፈጻጸም መለኪያዎች (Key Performance Indicators) ..... 45
6. አባሪዎች ..... 47

## ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

በሀገር ደረጃ የጥቃቅን፣ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራዞችን ልማት ለማፋጠን እና ኢንተርፕራይዞች በሀገር ኢኮኖሚ ያላቸውን ሚና ለማሳደግ እንዲሁም ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል በርካታ ስራዎችን ባለፉት ዓመታት ማከናወን የተቻለ ሲሆን በዚህም አበረታች ውጤቶችን ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን ይረዳ ዘንድ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ፣ የጥቃቅ፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ፖሊሲ፣ ስትራቴጅዎች እና የዘርፉ ልማት ማስፈጸሚያ ፍኖታ ካርታ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ የአቅም ልማት ስትራቴጂ፣ የተኪ ምርት ስትራቴጂ፤ የቆዳ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ስትራቴጂ፣ የትስስር ስትራቴጂ፣ የወጪ ንግድ ስትራቴጂ፤ የሽግግር ስትራቴጂ፤ የተግባቦት ስትራቴጂ፣ የኬሚካል ስትራቴጂ፣ የእንጨትና ፈርኒቸር ስትራቴጂ፣ የቴክኖሎጂና ኢንጅነሪንግ ስትራቴጂ፣ የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የተሞክሮ ቅመራና ማስፋት የአሰራር ስርዓት እንዲሁም የተለያዩ የኢንዱስትሪያላይዜሽን አቅም ልማት የማሰልጠኛ ማንዋሎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም 2.0፣ኢትዮጵያ ታምርት፣ የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽን እና ሌሎችንም ኢንሽየቲቮች በማዘጋጀት በየደረጃው አስፈፃሚና ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀት የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

በዚህ መሰረት ባለፉቱ አምስት ዓመታት ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በተደረገው ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የዘርፉን ኦኮኖሚ ድርሻ ከ6.9% ወደ 7.2%፣ የማምረት አቅም አጠቃቀምን ከ46% ወደ 65%፣ የአገር ውስጥ ምርት የገበያ ድርሻን ከ30% ወደ 46% ማሳደግ መቻሉን ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡

ይሁንና የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ችግር በአንድ ጊዜ ተፈቶ የሚያልቅ ጉዳይ ሳይሆን ተከታታይነት ባለው መልኩ ለቁልፍ ችግሮች መፍትሔ እየሰጡ መሄድ የሚያስፈልግ በመሆኑ፤ ከዚህ በፊት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በአራቱ ፓኬጆች ማለትም በኢንተርፕርነርሺፕ፤ በካይዘን፣ በቴክኖሎጂና በቴክኒካል ስልጠና ላይ በማትኮር ሲሰጥ የነበረው የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡበት ቢሆንም ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ከመስጠት እና የዘርፉን ችግር ሊፈታ በሚችል መልኩ ከመተግበር አንጻር ውስንነቶች ያሉበት በመሆኑ የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ በማካተት የአገልግሎት አሰጣጡ ኢንዱስትሪው አሁን ላይ ከሚፈልገው ድጋፍ

በመነሳት አገልግሎቱን በተሟላና ውጤታማ በሆነ መንገድ መስጠትን ዓላማ ያደረገ ሀገር አቀፍ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ስትራቴጂ የተዘጋጀ ሲሆን ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ይህ የኤክስቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.1.የቃላት ትርጓሜ

**"ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ነው

**"ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ማሽንን፣ መሣሪያን ወይም የሰው ኃይልን በመጠቀም ጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ የመጠን ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለው ምርት የሚያመርት ነው፤

**"ጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"፡-** ማለት እስከ 10 (አስር) ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና እስከ ብር 600,000 (ስድስት መቶ ሺ.ህ) ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

**"አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"፡-** ማለት ከ 11 (አስራ አንድ) እስከ 50 (ሃምሳ) ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 600,001 (ስድስት መቶ ሺ.ህ አንድ) እስከ ብር 10 ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን) ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

**"መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"፡-** ማለት ከ 51 (ሃምሳ አንድ) እስከ 100 (መቶ) ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 10,000,001 (አስር ሚሊዮን አንድ) እስከ 90 ሚሊዮን (ዘጠና ሚሊዮን) ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

**"የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት"**፡- ማለት የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ችግር የለየና በፍላጐት ላይ የተመሠረተ የተሟላ መረጃ የማደራጀትና የመስጠት፣ ሥልጠናና ምክር፣ ቴክኖሎጂ ልማት፣ ግብይት፣ የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያና ሌሎች መሰል ድጋፎችን መስጠትን እንዲሁም በተለያዩ ተቋማት የሚሠጡ አስፈላጊ ድጋፎችን ማመቻቸትን የሚያካትት ድጋፍ ነው፤

**"ተኪ ምርት"**፡- ከውጭ አገር የሚገቡ ምርቶችን በዋጋ፣ በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት ለመተካት በአገር ውስጥ የተመረተ ምርት ማለት ነው፤

**"ወጪ ንግድ"**፡- የውጭ አገር የገበያ መዳረሻን የምርት ደረጃ ባሟላ ሁኔታ በአገር ውስጥ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የተመረተ ምርት  ወደ ውጭ አገር መላክ ሲሆን ወደ ውጭ ለመሄድ በተዘጋጁ ማጓጓዣዎች ላይ ምርቶችን መጫንን ይጨምራል፤

**"የአቅም ልማት"**፡- ማለት ግለሰቦች፣ ተቋማት እና ማህበረሰብ ሁለንተናዊ እድገታቸውን በጊዜ ሂደት ሊያሳኳቸው ላሰቧቸው አላማዎች አስፈላጊና አስቻይ የሆኑ ቁሳዊ ሀብቶችንና የማይዳሰሱ ሀብቶችን (የእውቀት፣ የክህሎትና አመለካከት) የማግኘት፣ የማጠናከር፣ የመጠቀም እንዲሁም ጠብቆ የማቆየት ሂደት ነው፡፡

**"የገበያ ትስስር"**፡- ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የገበያ እድል ለመፍጠር ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፤ በሀገር ውስጥና በውጪ ሃገር ከሚገኙ አነስተኛ፤ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በግዢና ሽያጭ በጎንዮሽና በተዋረድ ግንኙነት የሚፈጠር የግብይት ሥርዓት ነው::

"የኢንዱስትሪ ክላስተር" ፦ በተቀራራቢ አካባቢ ተመጋጋቢ የአምራች ኢንዱስትሪ የሚሰባሰቡበት እና የግብዓት ምርት ትስስር ለመፍጠር፥ የሰው ኃይል ለመጠቀም፥ ለገበያ ተደራሽ ለመሆን እንዲሁም የቴክኖሎጂና ዕውቀት ሽግግር ለማሳለጥ በመተባበር እና በመደጋገፍ መንፈስ በመጠቀም ተወዳዳሪ ምርት የሚያመርቱበት አሰራር ነው፤

**"ብራንዲንግ"**፡- ማለት ምርትን/ አገልግሎትን በደንበኞችና በተጠቃሚዎች ዘንድ ልዩ እና መሳጭ ምስል በመፍጠር በገበያ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ዝነኛና ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲቆይ የማድረግ ሂደት ነው፤

**"ፈፃሚ አካላት"**፡- ማለት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት፣ በክልል ዘርፉን የሚመሩ ቢሮዎች፣ የዞን ወይም ክፍለ ከተማ አደረጃጀቱን የሚመሩ ጽ/ቤቶች፣ የወረዳ ወይም የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ወይም ጽ/ቤቶች፣ የክህሎት እና ስልጠና ተቋማት፣ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን እና  በየደረጃው ያሉ ዘርፉን የሚደግፉ አካላትን ያጠቃልላል፡፡

**"እሴት ሰንሰለት"፡-** ማለት የአንድን ለገበያ የሚቀርብ ምርት ከግብዓቱ ጀምሮ እስከ ፍጆታ (ጥቅም ላይ እስከዋለበት ጊዜ) ድረስ ያሉና ለምርት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገሮች የሚቀነባበሩበት ዓላማ መር ቅደም ተከል ማለት ነው

**"የማምረት አቅም አጠቃቀም"፡-** አንድ ተቋም ወይም ድርጅት ያሉትን የተለያዩ ግብዓቶች በምን ያህል የብቃት ደረጃ ተጠቅሞ የታለመለትን ምርት ወይም ውጤት አሳክቷል የሚለውን የምንለካበት ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካች ሲሆን ልኬቱም በመቶኛ የሚገለጽ ነው፡፡

**"የኢንተርፕራይዝ የእድገት ደረጃ ሽግግር"፡-** ማለት አንድ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የራሱን ጥረት እና የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በሰው ሀይል፣ በጠቅላላ ሀብት መጠን፣ በገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ የሽግግር መስፈርት በማሟላት መሸጋገር ሲችል ነው፡፡

**"የጋራ መገልገያ" ፡- ለ**ኢንተርፕራይዞች ምርታማነት የምርት ጥራትና ተወዳዳሪነት አስተዋፅዖ ያላቸውና ኢንተርፕራይዞች በተናጠል ሊያሟሏቸው የማይችሏቸውን አስፈላጊ መሰረተ-ልማቶች፣ ቴክኖሎጂዎች፣ ማሽነሪዎች፣ የማሰልጠኛ ማዕከላት፣ የመፈተሻ መሳሪያዎች፥ ቤተ-ሙከራ፣ ካፍቴሪያ፣ የምርምር ማዕከላት የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል አገልግሎት ማለት ነው፤

**"ቴክኖሎጂ"** ፦ አምራች ኢንተርፕራይዞች ለማምረት የሚጠቀሙባቸው ማሽኖች፣ የቴክኒክ ሂደቶች፣ ዘዴዎች ወይም ዕውቀቶች ነው፤

**"ሞዴል ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"፡-** በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተሰማርቶ ተወዳዳሪ ምርት በማቅረብ ለላቀ ውጤት የበቃና ለሌሎች መሰል ኢንተርፕራይዞች አርአያ በመሆን በማስፋት ስትራቴጂ ላይ ግንባር ቀደም የልማት ሀይል የሆነ ኢንተርፕራይዝ ነው፣

**"ሰርኩላር ምርት ስርዓት"** ፦ በዘላቂና አካታች ኢንዱስትሪ ልማት ውስጥ የምርት ግብይት ስርዓት ሲሆን በማምረት ሂደት ውስጥ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ከጥሬ ዕቃ ማምረቻ እስከ ምርት ማከማቻ፣ አቅርቦት እና በመካከላቸው ያለውን እያንዳንዱን የመጓጓዣ ግንኙነት አካባቢያዊ እና ሰብአዊ ተፅዕኖን ከግምት ውስጥ ማስገባትን ያካትታል፡፡

## 1.2.የማንዋሉ ህጋዊ መሰረት

ይህ ማንዋል እንዲዘጋጅና ወደ ትግበራ ለማስገባት የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 21(1) ሰ መሰረት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ለኢንዱስትሪ ሚንስቴር የተሰጠው በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 526/2015 አንቀጽ 5(7) በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልገሎት ተደራሽ እንዲሆን የመተግበር እና የማስተባበር ስልጣን ያለው በመሆኑ እንዲሁም ስራው በ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ውስጥ የተያዘ፣ ረቂቅ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ስትራቴጂ የተዘጋጀለት እና በአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲው ውስጥ የተካተቱ ድጋፎችን ተፈፃሚ ለማድረግ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን የሚፈልጉ በመሆኑ ይህ ማንዋል ህጋዊ መሰረት ያለው ነው፡፡

## 1.3. የማንዋሉ ዓላማ

የጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የምርት ጥራትና ምርታማነት በማሳደግ በዘላቂነት በሃገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ዲጂታል፣ የተቀናጀ፣ ቀልጣፋ እና ሁሉን አቀፍ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የሚያገኙበትን ግልጽና ተቀራራቢነት ያለው የአሰራር መዘርጋት ነው፡፡

## 1.4.የማንዋሉ አስፈላጊነት

- ቀደም ሲል ለመካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ ሲሰጥ የነበረው ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽ አገልግሎት ማስተግበሪያ ሰነድ በመሆኑ፤ የመካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንርፕራይዞችን ያካተተ ግልጽ አሠራር ስርዓት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤
- የኢንተርፕራይዞችን ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፤ የገበያ ተወዳዳሪነት የሚያረጋግጥ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

- የዘርፉ አስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት ለጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡትን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጤታማነት ለማሻሻል ግልፅ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት እና የማስፈጸሚያ ሰነድ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፣

## 1.5. የማንዋሉ መርሆዎች

ይህ ማንዋል የሚከተሉት መርሆዎች መሰረት የሚተገበር ይሆናል

- ፍላጎትንና ክፍተትን መሰረት ያደረገ ዉጤታማና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት መስጠት፤
- የተቀናጀ፣ድግግሞሽኝ ያስወገደ፣ ወጭ ቆጣቢ እና ተደራሽ የሆነ አገልግሎት መስጠት፤
- የግል ዘርፍ ተሳትፎ የሚያጠናክር፣
- ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን የሚያልቅ
- ለቴክኖሎጂ ልማት እና ሽግግር ቅድሚያ የሚሰጥ

## 1.6.የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ማንዋል በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በአገልግሎቱ በዕድገት ተኮር ንዑስ ዘርፎች የተሰማሩ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እና ዘርፉን ከመደገፍ አኳያ ለሚመለከታቸው ተቋማት በህግ በተሰጣቸው ተግባርና ሃላፊነት መሰረት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡ ፡

## 1.7.የማኑዋሉ ተጠቃሚዎች

የአሰራር ማንዋሉ ተጠቃሚዎች በዕድገት ተኮር ንዑስ ዘርፎች የተሰማሩ ጥቃቅን፥ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ሲሆኑ ይህም ፍላጎትና ክፍተትን መሠረት ያደረገ ለዕድገት ደረጃቸው የሚመጥን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። በሌላ በኩል በየደረጃው የሚገኙ የዘርፉ ልማት አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ በመስጠት የዘርፉን ልማት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሳደግ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ስለሚያስችላቸው የዚህ ማኑዋል ተጠቃሚ ናቸው።

## 1.8.የሚጠበቅ ውጤት

የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ ማንዋል በመተግበር በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አጀንዳዎችን፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን እና የዘርፉን ስትራቴጂክ ዕቅድ በማሳካት የሚከተሉትን ውጤቶችን ማስመዝገብ ይጠበቃል፡፡

- የተሻሻለ የማምረት አቅም አጠቃቀም
- የተሻሻለ የምርት ጥራት፣ ምርታማነትና ተወዳዳሪነት
- ያደገ የውጭ ምንዛሬ ግኝት
- ያደገ የአገር ውስጥ ገበያ ድርሻ
- ያደገ የተኪ ምርት መጠንና የገበያ ድርሻ
- ያደገ የስራ ዕድል ፈጠራ
- ያደገ የደረጃ ሽግግር ያደረጉ ኢንተርፕራይዞች

# ክፍል ሁለት

## 2. የምሰሶዎች እና የተግባራት ትስስር ማዕቀፍ/Framework/

### 2.1.የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ምሰሶዎች

- ምቹ ምህዳር መፍጠር /Enabling Environment/
- እውቀት እና ክህሎት /Knowledge and Skills/
- መሬትና መሰረተ ልማት /Infrastructure/
- የፋይናንስ አቅርቦት /access to Finance/
- የግብዓት አቅርቦት /Access inputs/
- የቴክኖሎጂ ልማት፣ ሽግግር እና ፈጠራ /Technology Development, transfer & Innovation/
- የገበያ ተወዳዳሪነት /Market Access and Competitiveness/
- ከባቢያዊ እና ማህበራዊ ደህንነት /Environmental & Social Safeguards/

#### 2.1.1. የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ምሰሶዎች እና ዋና ዋና ተግባራት

| ተ.ቁ | ምሰሶዎች | ዋና ዋና ተግባራት | የሚሰጡ ድጋፎች |
|---|---|---|---|
| 1 | ምቹ ምህዳር መፍጠር | • የተቋማትን አቅም ማሳደግ<br>• ባለሙያዎችን አቅም ልማት ማሳደግ<br>• ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት መዘርጋት<br>• ተቋማት አደረጃጀት መፍጠር | • የፈፃሚና የአስፈፃሚ አካለትን የመፈፀም አቅም ለማሳደግ አሰራሮችን ማዘመን፤ የአንድ መስኮት አገልግሎት መተግበር፤ኢንተርፕራይዙን ሊደግፍ የሚያስችሉ የድጋፍ ማዕቀፎችን፣ የአሰራር ማንዋሎችን በማዘጋጀት ተደራሽ ማድረግ<br>• ያሉ ውስን ሀብቶችንና የሰው ሀይልን መሰረት ያደረገ ድግግሞሽን ሊያስቀር በሚችል መልኩ በተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | መዘርጋት(የትብብር ማዕቀፍ ማዘጋጀት)<br>• አገልግሎቱን ተደራሽ እንዲሆንና ጥራቱን የጠበቀና ተቋማት ሚናቸውን ለመወጣት ያስችል ዘንድ ውጥነት ያለው አደረጃጀት መፍጠር(ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ስትሪንግ ኮሚቴ ማቋቋም) |
| 2 | የእውቀት እና የክህሎት | • በቴክኒክና ሙያ ተቋማት እና በዩኒቨርሲቲዎች የሚዘጋጁ የስልጠና ካሪኩለሞች የኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ<br>• የቴክኒክ ስልጠና መስጠት<br>• የንድፈ ሀሳብ ስልጠና መስጠት<br>• ጥናት እና ምርምር<br>• በትምህርትና ምርምር ተቋማትና በኢንዱስትሪ መካከል ቅንጅት እንዲፈጠርና እንዲጠናከር ማድረግ፤<br>• ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና የሚሰጥበት ስርዓት መዘርጋት | • የኢንዱስትሪው የሚፈልገውን የሰው ሀይል ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ<br>• አጫጭር ስልጠናዎችን ለመስጠት የሚያስችል ካሪኩለም ና የሙያ ስልጠና ፓኬጆችን ማዘጋጀት፣ከዚህ በፊት የተዘጋጁትን ወቅታዊ ማድረግ እንዲሁም የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን ከዩኒቨስቲዎች ጋር እንዲሰራ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ<br>• ለኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ክፍተታቸውን መሰረት ያደረገና የኢንዱስትሪውን የማምረት አቅም የሚያሻሽሉ የንድፈ ሀሳብና የቴክኒካል ስልጠናዎችን መስጠት፤ የስራ ላይ ስልጠና ማካናወን<br>• በምርምርና ትምህርት ተቋማት( ዩኒቨስቲዎች፣ የምርምር ማዕከላትና የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች እንዲሁም በአስፈፃሚና ፈፃሚ ተቋማትና በኢንዱስትሪዎች መካከል ትስስር በማጠናከር አዳዲስ ምርቶችን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | እንዲመረቱ፤ በኢንዱስትሪው ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን ጥናትና ምርምር በማድረግ ግኝቶችን ማስተላለፍ<br>• የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በስራቸው ያሉ ባለሙያዎችን የመፈፀም አቅም ለማሳደግ ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠናዎችን መስጠት ( የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ማካሄድ፤ ስልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ አሰልጠኝ መምረጥ/ማዘጋጀት/ ስልጠና መስጠት እና የመጣውን ለውጥ መገምገም |
| 3 | መሬትና መሰረተ ልማት | • የመስሪያና የመሸጫ ቦታ ማልማት እና ማመቻቸት<br>• የመሬት አቅርቦት ማመቻቸት<br>• የኤሌክትሪክ አገልግሎት<br>• የውሃ፣የስልክ፣ የመንገድ፥ የኮሙኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶች እንዲያገኙ ድጋፍ ማድረግ<br>• ሎጀስቲክ አግልግሎት | • የመሬት አቅርቦትን ለኢንዱስትሪው የሚስፈልገውን ከከተማ አስተዳደሮችና ከሚመለከተው የስራ ክፍል ጋር በቅንጅት ተቀራርቦ ከሶስተኛ ወገን ነፃ እንዲሆን በማስቻል ፍትሀዊ በሆነ መልኩና የአካባቢን ፀጋ መሰረት ባደገ መልኩ እንዲለማ ማድረግ<br>• የሚገነቡ የኢንዱስትሪ ክላስተሮች የግል ና የመንግስት የጋራ ልማትን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ግንዛቤ በማስጨበጥ ወደ ተግባር ማስገባት<br>• አዳዲስ የሚገነቡና በስራ ላይ ያሉ ክለስተር ሼዶች የጥራት መስፈርትን እንዲያሚሉ አሰራር መቀየስና የምርቶችን ባህሪና አመራረታቸውን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ማስቻልና ለተጠቃሚው ማድረስ<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት ለኢንዱስትሪው የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ እንዲደረጉ የጋራ መድረክ ማዘጋጀት አፈፃፀሙን መከታተል |
| 4 | የፋይናንስ አቅርቦት | • ሊዝ ፋይናስ አገልግሎት<br>• የስራ ማሰኪጂያ ፋይናንስ አገልግሎት<br>• የብድር ዋስትና<br>• የቢዝነስ ፕላን እና ፕሮጀክት ፕሮፖዛል<br>• የሂሳብ መዝገብ አያያዝ<br>• ቁጠባ ባህል ማዳበር<br>• ኢኖቬቲቭ የፋይናንስ አማራጮች ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፤ | • አዳዲስ የፋይናንስ ምንጮች ማበራከት<br>• የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ሊደግፍ በሚያስችል መልኩ የፋይናንስ ተቋቋማት የአገልግሎት መስጫ መስኮቶችን ማጠናከር ፣የብድር መስጫ መንገዶችን ማስፋት፣የጥቃቅን ፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ባንክ እንዲቋቋም ማስቻል<br>• የቢዝነስ ፕላንና ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ተደራሽ ማድረግ፣ የማማከር ስራ መስራት<br>• የቁጠባ ባህል እንዲዳብር ግንዛቤ በማስጨበጥ የቆጣቢ ቁጥርን ማበራከትና ለሌሎች የስራ ማስኬጃ ብድር ማመቻቸት<br>• የብድር ዋስትና መንገዶችን የዘርፉን ባህሪ ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲሆን ጥናት በማድረግ አዳዲስ ስርዓት መዘርጋት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | የግብዓት አቅርቦት | • የሀብት ምንጭ፣ የአካባቢ ጸጋ እና የግብዓት መረጃ መስጠት<br>• የግብዓት ትስስር መፍጠር<br>• የእሴት ሰንሰለት መሰረት ያደረገ ድጋፍ ማድረግ<br>• የግብዓት-ምርት ጥምርታ | • የአካባቢ ፀጋ በመለየትና መረጃ በማደራጀት ለተጠቃሚ ኢንተርፐራይዞች ማሰራጨት<br>• ግብአት ትስስር ለማድረግ የግብአት አቅራቢ ተቋማት መረጃ በማደራጀት ( ከነጋዴዎች፤ከአምራቾች፤ ከዩኒየኖችና ቀጥታ ከአርሶ አደሩ) ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ መደገፍ፣ አፈፃፀሙን መከታተል፣መረጃ ማደራጀት<br>• የእሴት ሰንሰለት መሰረት ያደረገ ጥራቱን የጠበቀ ግበአት አቅርቦት እንዲቀርብ ግንዛቤ መፍጠር፣ክትትል ማድረግ<br>• ግብኣት ምርት ጥምርታን መሰረት ያደረገ አቅርቦት እንዲኖር አሰራር መዘርጋት |
| 6 | የቴክኖሎጀ ልማት እና ሽግግር እና ፈጠራ | • የእሴት ሰንሰለትን መሰረት ያደረገ ቴክኖሎጂ ማልማት፣መቅዳት፣ ሽግግር ማደረግ<br>• የማምረት አቅም እና ምርታማነት የሚያሳድጉ የአሰራር ሰርዓቶችን (ሊን ማኑፋክቸሪንግ፣ ካይዘን፣ ሲክስ ሲግማ፣ የጥራት ስራ አመራር ….) ተግባራዊ ማድረግ<br>• ከቴክኖሎጂና ምርምር ተቋማት ጋር ትስስር መፍጠር (ዩኒቨርስቲ፣ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት፤ የቴክኖሎጂ ልህቀት ማዕከላት) | • የማምረት አቅምና ምርታማነትን ለማሳደግ የበኢንተርፕራይዙ ያሉ ችግሮችን በጥናት/diagnosis/ መለየት ለችግሮች መፍትሔ መስጠት<br>• አዳዲስ አሰራሮችን ( ካይዘን፤የጥራት ስራ አመራር ፣ሊን፣ ሲክስ ሲግማ እና ሌሎችን) እንዲተገብሩ ድጋፍ በማድረግ የመጣውን ለውጥ መገምገም<br>• አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት፣ በመቅዳት ለተጠቃሚዎች በፕሮቶታይፕ ምርት በማዘጋጀት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | • ቴክኖሎጂ/ኢንዱስትሪ 4.0 እንዲጠቀሙ ማበረታታትና መደገፍ<br>• የጋራ መገልገያ ቴክኖሎጂ መጠቀም /common facility center | ማስተላለፍና እንዲበራከት ወደ ገበያ እንዲገበ መደገፍ<br>• የጋራ መገልገያ ቴክኖሎጂዎች በየክላስተሩ እንዲደራጁ በማድረግ ወጪ ቆጣቢ ና ጊዜን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲጠቀሙ አሰራሮችን መቀየስ፣ ድጋፍ ማድረግ ፣ መከታተል<br>• ወቅቱን የዋጁ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አዳደዲ አሰራሮችን ማስተዋወቅ |
| 7 | የገበያ ተደራሽነትና ተወዳደሪነት | • የምርት ደረጃ እንዲወጣላቸው ማድረግ<br>• ኢንተርፕራይዞችን የምርት ጥራት ሰርተፊኬሽን እንዲያገኙ መደገፍ/መስጠት<br>• ምርቶች ብራንድ እንዲኖራቸው (በስም፥ በሎጎ፥ በዲዛይን እና በሚሰጡት አገልግሎት በደንበኞች አዕምሮ ውስጥ የተለዩ እንዲሆኑ) ማድረግ<br>• በሀገር እና አለም አቀፍ ኤግዚቢሽንና ባዛር እንዲሳተፉ ማድረግ<br>• የገበያ ትስስር መፍጠር<br>• ዲጅታል ገበያ አገልግሎት መስጠት<br>• የሀገር ውስጥ እና የውጪ አገር የገበያ መዳረሻ መረጃ ተደራሽ ማድረግ<br>• በአፍሪካ ነጻ ገበያ ላይ ተሳታፊ ማድረግ<br>• እሴት ጭማሪ | • ኢንዱስትርውን ታሳቢ ያደረገ ደረጃ ያልወጣላቸውን ምርቶች በመለየት ደረጃ እንዲዘጋጅላቸው ከሚመለከተው ተቋም ጋር በጋራ መስራት<br>• የምርት ጥራት ስርተፍኬሽን እንዲያገኙ የማማከር፣ስልጠና የመስጠትና የመደግፍ ስራዎችን ተደራሽ ማድረግ<br>• አስገዳጅ የሆኑ ምርቶች የሮርትፊኬሽን በማድረግና የደረጃ ምልክትን እንዲጠቀሙ ማስቻል<br>• የተዘጋጁ ስኪሞች ተግባራዊ እንዲደረጉ ክትትልና ድጋፍ መስጠት<br>• ምርቶቻቸውን የሚያስተዋውቁበት አሰራር መዘርጋት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | • በግብይት ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት ስልጠና መስጠት<br>• የዲጅታል ገበያ ፕላትፎርም በመዘርጋት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል<br>• የገበያ መዳረሻን በጥናት በመለየት ተደራሽ ማድረግ |
| 8 | የአካባቢ እና ማህበራዊ ደህንነት | • የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት<br>• የአረንጓዴ ማኑፋክቸሪንግ፥ ሰርኩላር ኢኮኖሚ ወዘተ ክሊነር ምርት አመራረት አገልግሎት<br>• የኢነርጂ አጠቃቀም<br>• የሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞች አካታችነት<br>• የስራ ላይ ደህነት<br>• ማህበራዊ ጥበቃ | • በማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በምርት ሂደት<br>• የሀይል ቁጠባን ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ፡በማስቻል የሀይል ብክነትን ማስቀረት<br>• በሚደረጉ ድጋፎች፣ ስልጠናዎችና ሌሎች አገልግሎቶች የሴቶችን፣ ወጣቶችንና አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ በዕቅድ ተይዞ ተጠቃሚ ማድረግ<br>• የስራ ላይ ደህንነት በተመለከተ የአቅም ግንባታ ስራዎች መስራት፣ማረጋገጥ<br>• ማህበራዊ ጥበቃ በሁሉም ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲተገበር ግንዛቤ ማስጨበጥና አፈፃፀሙን መከታተል |

#### 2.1.1.1. ምቹ አከባቢን መፍጠር /Enabling Environment

ይህ የኢንዱስትሪ አክስቴሽን አገልግሎት ምሰሶ አግልግሎትን ለመስጠት መሰረት ሲሆን ተቋማት የመመስረትና የማጠናከር፣ ቅንጅታዊ አሰራርን የመፍጠር፣ የተቋማትን አደረጃጀትን የመፍጠር፣ የአሰራር ስርዓትን የመዘርጋት፣ ስትራቴጂዎችን፣ መመሪያዎችንና ማንዋሎችን

የማዘጋጀት፣ አግልግሎት የሚሠጡ ባለሙያዎችን የመለየትና የአቅም ልማት ማከናወንን ያጠቃልላል፡፡

- ✓ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ለመስጠት የሚስችል በፌዴራል፣ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች መዋቅር፣ አደረጃጀትና ቅንጅት እንዲፈጠርና እንዲጠናከር ይደረጋል፤
- ✓ አገልግሎቱን ተግባራዊ ለማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ የማስፈፀሚያ ሰነዶችን (ማንዋሎች) በማዘጋጀት ተፈፃሚ ይሆናል፤
- ✓ ተቋማት የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ለማስተግበር በሚያስላቸው ሁኔታ አቅማቸው ይገነባል፤
- ✓ ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የሚሰጡ የግል ተቋማት እንዲበራከቱና እንዲጠናከሩ ተገቢው ድጋፍ ይደረጋል፤
- ✓ አገልግሎቱን ለማስቀጠልና በተሻለ መልኩ ለመፈፀም የሚያስችል የሀብት ማፈላለግ ስራ ይከናወናል፣ የራሱ በጀት እንዲመደብለት ይደረጋል፤
- ✓ የአገልግሎት ወጪን በተመለከተ በወጪ መጋራት አሰራር የሚተገበር ይሆናል፤ ታሳቢ ሊደረግ ይችላል፡፡
- ✓ የክትትልና ድጋፍ እና ምዘና ስርዓት ይተገበራል፤

### 2.1.1.2. የቴክኖሎጆ ልማት እና ሽግግር እና ፈጠራ

ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ኢንተርፕራይዞች ውስብስብ ችግሮችን እንዲፈቱ፣ ምርታማነትን እንዲያሳድጉ እና በየጊዜው በሚሻሻል የገበያ ቦታ ላይ ተወዳዳሪነት እንዲኖራቸው በማስቻል ለእድገታቸው የማይተካ ሚና ይጫዎታል፡፡

የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ድጋፉ የቴክኖሎጂ ክፍተቶችን (ቁሳዊ፣ ዕውቀታዊ፣ ሰነዳዊ፣ ድርጊታዊ) በመለየት መፍታት ላይ የሚያተኩር ሲሆን አገልግሎቱን በመስጠት ሂደት የኢንተርፕራይዞችን ቴክኖሎጂ የመቀበል እና የመጠቀም አቅም የመለየት፥ ቴክኖሎጂን ከመጠቀም አኳያ ኢንተርፕራይዞች ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ የማወቅ እንዲሁም ያላቸውን የሰው ሀይል

አቅም፣ የሚጠቀሙትን ማሽኖችንና መሣሪያዎች፣ ተቋማዊ አዳረጃጀት፣ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም የማየትና የመገምገም ስራ ይከናወናል፡፡

ከኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አኳያ የቴክኖሎጂ ልማት ሽግግርና ፈጠራ ስራችን በሚከተሉት አንኳር ጉዳዮች ላይ በማጠንጠን የሚከናወን ይሆናል፡፡

- የቴክኖሎጂ ሽግግር አስፈጻሚ አካላት የቴክኖሎጂ ልማት ሂደት የእሴት ሰንሰለት ትንተና መሰረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ፣
- የቴክኖሎጂ ማልማትና ማሸጋገር ሂደት የሀብት ብክነትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ድግግሞሽን በማስቀረት ቴክኖሎጂዎች በጥናትና ምርምር የሚለዩበት፤ የሚመረጡበት፤ የሚለሙበት፤ የሚፈተሹበትና ለኢንተርፕራይዞች የሚያሸጋገሩበት ወጥና የተማከለ አሰራር እንዲኖረው ማድረግ፣
- በጥናትና ምርምር ተቋማት፣ የቴክኖሎጂ አልሚዎች፤ የሀገር በቀል ዕውቀት አልሚዎችና ኢንተርፕራይዞች መካከል ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል
- የግሉ ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎችን በማከናወን እና በመደገፍ ረገድ ያለውን ሚና በቀጣይነት እያደገ እንዲሄድ ማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፡፡
- ምርታማነትንና ተወዳዳሪነትን የሚያሳድጉ እንደ ሊን ማኑፋክቸሪንግ፥ ካይዘን፥ የጥራት ስራ ዓመራር የመሳሰሉ ኢኖቬቲቭ ስርዓቶች እንዲተገበሩ መደገፍ፤

#### 2.1.1.3. መሠረተ ልማት

የዘርፉን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማሳደግ ረገድ ወሳኝ ሚና ከሚጫወቱ አገልገሎቶች መካከል መሰረተ ልማትን ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ተደራሽ ማድረግ ይገኝበታል፡፡ ከዚህ አኳያ ኢንተርፕራይዞች በዘላቂነት ሊያመርቱ የሚችሉበት መሰረተ ልማት የተሟላለት የማምረቻ ቦታ ማልማት፣ በተናጥል የሚቀርቡ የመሰረተ ልማት ጥቄዎችን ማሟላት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት፡-

- እንደ ከተሞቹ የእድገት ደረጃ ማስተር ፕላን መሠረት ያደረገ መሰረተ ልማት የተሟላለት የማምረቻ፥ ማሳያና መሸጫ ቦታ ይዘጋጃል፤ የሚለሙበትን አማራጭ በመለየት እንዲገነቡ ይደረጋል፤
- የኢንተርፕራይዞችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የመንገድ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የውሃ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እንዲሟላ ይደረጋል፤
- ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁና በተናጠል ለማሟላት የሚከብዱ ቴክኖሎጂዎችንና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን ያካተተ የጋራ መገልገያዎች እንዲለሙ ይደረጋል፤
- ፈጠራን የሚያበረታቱ የኢንኩቤሽን ማዕከላት እንዲደራጁ ይደረጋል

#### 2.1.1.4. የገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነት

የኢንተርፕራይዞች ምርት ወይም አገልግሎት ለሀገር ውስጥና ለውጪ ሀገር ገበያ በቀላሉ ተደራሽ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ኢንተርፕራይዞች እርስ በእርስ ግብይት እንዲፈጥሩ በማድረግ፤ በሀገር ውስጥ እና አለም አቀፍ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች እንዲሳተፉ በማድረግ፤ የዲጂታል ፕላት ፎርምን በመጠቀም ምርትና አግልገሎታቻን እንዲያስታዋውቁና እንዲሸጡ በማድረግ፣ የገበያ መዳረሻ መረጃዎችን እንዲያገኙ በማስቻል፣ በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ላይ የሚሳተፉበትን ሁኔታ በመፍጠር የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ከገበያ ተደራሽነት ጎን ለጎን የኢንተርፕራይዝ ምርቶች በጥራት፣ በዋጋ፣ በመጠንና በአቅርቦት ጊዜ እንዲሁም አዳዲስ የፈጠራ ሀሳቦች በማመጨት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

- የኢንተርፕራይዝ ምርቶች በሀገር ውስጥና በውጪ አገር ገበያ ያላቸውን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ከብራንዲንግ፣ፓኬጂንግ፣ የምርት ደረጃ ሰርተፊኬሽን ጋር የተያያዘ አገልግሎት ተደራሽ ይደረጋል፤
- በቀጠናዊ፥ አህጉራዊና ሌሎች የንግድ ስምምነቶች መሰረት ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሰራል፤
- በመንግስት ግዢ አሰራር ኢንተርፕራይዞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ፤
- የምርት ማሳያና መሸጫ ቦታዎች እንዲስፋፉ ይደረጋል፤

- ኢንተርፕራይዞች በሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ በወጪ መጋራት መርህ እንዲሳተፉ ይደረጋል፤
- ከሸማች ህብረት ስራ ማህበራት ሱቆች ጋር በማስተሳሰር፣ በምርት መሸጫና ማሳያ ማዕከላት ምርቶቻውን እንዲያስተዋውቁና እንዲሸጡ በማድረግ እና በኤሌክትሮኒክስ ፕላት ፎርም ተጠቅሞ የተሳለጠ ግብይት እንዲፈጥሩ በማድረግ የገበያ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡
- ኢንተርፕራይዞች የገበያ ዕድሎችን በጋራ መጠቀም የሚችሉበት የእርስ በእርስ ትስስር እንዲፈጥሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤

#### 2.1.1.5. ግብዓት አቅርቦት

የግብዓት አቅርቦት ችግር ዘርፉ በሚጠበቅበት ፍጥነት እንዳያድግና አምራቾች ከማምረት አቅማቸው በታች እንዲያመርቱ ምክንያት በመሆን ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ በዘርፉ የእሴት ሰንሰለት ተመጋጋቢነት እና በአምራች ኢንተርፕራይዞች መካከል የግብዓትና ምርት ትስስር ውስንነት የሚታይ በመሆኑ እንደ አገር ከአምራች ኢንተርፕራይዝ ዘርፉ ሊገኝ የሚገባውን ጥቅም ማግኘት አልተቻለም፡፡

የኢንተርፕራይዞችን የግብዓት ችግር ለመፍታትና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል ከግብዓት አቅርቦት አኳያ የሚከተሉት ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል፡፡

- የኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪ ትስስር ስትራቴጂ መሰረት የግብዓት ትስስር ላይ ያለውን የጎንዮሽ፣ የኋልዩሽ ፣የፊትዩሽ እና የአቀበታዊ ትስስር ችግር ለመፍታት የሚያስችል የአስራር ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
- ዋና ዋና የግብዓት አቅራቢዎችን/ምንጮችን በመለየት፥ የአገር ውስጥ ግብዓት አምራቾችን በማበረታታት ከኢንተርፕራይዞች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ማስቻልና የተጠናከረ የግብዓት አቅርቦት ሰንሰለት መፍጠር፤
- በግብዓት ግዥ ሂደት የኢንተርፕራይዞች የመደራደር አቅም እንዲያድግ፥ በተነፃፃሪ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲገዙና የትልልቅ አቅራቢዎችን/አምራቾችን ዝቅተኛ የግብዓት ትዕዛዝ መጠን (minimum order quantity) ማሟላት እንዲችሉ በጋራ ተቀናጅተው ግብዓት የሚገዙበት አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፤

- ለግብዓት ግዥ የሚውል ብድር አቅርቦት አሰራር ስርዓት (input credit scheme) ተግባራዊ እንዲደረግ ይሰራል፤
- ግብዓት አምራቾችና አቅራቢዎችን፣ የሚያቀርቡት ግብዓት ዓይነትና መጠን ወዘተ መረጃ በመለየትና በማደራጀት ተደራሽ ይደረጋል።
- የግብዓት ብክነትን በሚቀንስና ውጤታማ በሆነ መንገድ መጠቀም በሚችሉበትና ጥራት ያላቸውን ግብዓቶች በሚያገኙበት ሁኔታ ስልጠናና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል።

### 2.1.1.6. እውቀት እና ክህሎት

የአቅም ልማት ግለሰቦች፣ ተቋማት እና ማህበረሰብ ሁለንተናዊ እድገታቸውን በጊዜ ሂደት ሊያሳኳቸው ላሰቧቸው አላማዎች አስፈላጊና አስቻይ የሆኑ ቁሳዊ ሀብቶችንና የማይዳሰሱ ሀብቶችን (የእውቀት፣ የክህሎትና አመለካከት) የማግኘት፣ የማጠናከር፣ የመጠቀም እንዲሁም ጠብቆ የማቆየት ሂደት ነው። በኢንዱስትሪው ውስጥ ለመስራት የኢንዱስትሪውን ውስብስብ ባህሪ ታሳቢ ያደረገና በየጊዜው ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር እያደገ የሚሄድ ዕውቀትና ክህሎት ይፈልጋል።

**ሀ. እውቀት**

የንድፈ ሃሳብ እውቀት ግለሰቦች እና ማህበረሰቦች ለውጥን እንዲቆጣጠሩ፣ እንዲተባበሩ እና በኢንዱስትሪ አካባቢ በብቃት እንዲሰሩ ያግዛል። የኢንተርፕራይዙን እድገት በቀጣይነት ለማረጋገጥ የኢንተርፕራይዙ አመራሮችና ሰራተኞች በሚከተሉት ጉዳዮች የንድፈ ሃሳብ እውቀት ያገኛሉ።

በኢንዱስትሪ አመራር እና አስተዳደር፣ በተግባቦት ፣ ፈጠራና አስተሳሰብ ፣ ውሳኔ አሰጣጥ፣ በቡድን ስራ እና ትብብር፣ በአደጋ ስራ አመራር፣ የደንበኞች አገልግሎት፣ የመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች፤ ማበረታቻዎችና ሌሎችም ላይ ያላቸውን ዕውቀት ለማሳደግ የንድፈ ሀሳብ ስልጠና ይሰጣል።

**ለ. ክህሎት**

የተግባር ተኮር ክህሎት በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን የአቅም ግንባታ ቁልፍ ተግባር ሲሆን ግለሰቦች እና ድርጅቶች ማሽነሪዎችን ለማንቀሳቀስ፣ የምርት ሂደቶችን ለመምራትና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የሚስችላቸው ነው፡፡ ይህ ክህሎት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ጥራትን ለማረጋገጥ እና ፈጠራን ለማዳበር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም የማምረት ሂደቶች እና ልዩ ቴክኒካዊ ክህሎቶች፣ የመሳሪያ አሠራር እና ጥገና፣ የቢዝነስ ዕቅድ እና የፋይናንስ አስተዳደር፣ የኢንተርፐርነርሺፕ፣ የምርት ልማት እና ፈጠራ፣ የፕሮጀክት ስራ አመራር፣ የአዋጭነት ጥናቶች፣ የምርት ደረጃና ጥራት ስራ አመራር ሂደትና ሌሎችንም ስልጠናዎች የሚያጠቃልል ነው፡፡

ከአቅም ልማት ጋር በተያያዘ የሚሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት የኢንተርፕራይዞችን የክህሎትና ዕውቀት ችግር ከመፍታት ባለፈ ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሸጋግርና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ዕድገት የሚያመጣ እንዲሆን በሚከተለው አግባብ የሚተገበር ይሆናል፡፡

- ኢንተርፕራይዞች የምርት ጥራትና ምርታማነትን ለማሻሻል የሚረዳ እውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው በዘርፉ ክህሎትና ልምድ ባላቸው የመንግስት አገልግሎት ሰጪዎች/አማካሪዎች አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፤
- ወጪን ከመቆጠብ ባሻገር የአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነት ለማሻሻል የአቅም ልማት ስልጠናም ሆነ ምክር አገልግሎት በዲጅታል አማራጮች ለተጠቃሚዎች የሚቀርቡበት ሁኔታ ይመቻቻል፤
- የአቅም ልማት ስልጠና በአምራች ኢንዱስትሪ የአቅም ልማት ስትራቴጂው እና የማስተግበሪያ የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት እንዲተገበር ይደረጋል፤
- የአቅም ልማት ስራው ወቅቱን የዋጀ፣ የአዲሱ ትውልድ የቴክኖሎጂ አብዮት እና ተለዋወጭ የገበያ ባህሪን ታሳቢ ያደረገና ተለማጭ የአሠራር ስርዓትን የሚከተል እንዲሆን ይደረጋል፤
- የአቅም ልማት ስራችን በኢንተርፕራይዞች የስራ ቦታ ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ፥ በዘርፉ ተጨባጭ ልምድ ያላቸውን አማካሪዎች ከኢንተርፕራየዕዞች ጋር በማገናኘት፥ እርስ በእርስ ግንኙነትን በማመቻቸትና ልምድ እንዲለዋወጡ በማድረግ ይፈፀማል፡፡

- ዘርፉ የሚፈልገውን የእውቀትና ክህሎት ፍላጎት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሟላት የኤክስቴንሽን ድጋፍ የሚሰጡ ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶች ተከታታይነት ባለው ሁኔታ አቅማቸው የሚገነባበት አሰራር ይተገበራል፤
- የኢንተርፕራይዞች እና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች አቅም የሚገነባባቸው ማዕከላት እንዲቋቋሙና ወደ ስራ እንዲገቡ ይደረጋል።

### 2.1.1.7. የፋይናንስ አቅርቦት

የፋይናንስ አቅርቦት ለኢንተርፕራይዞች ዕድገት፥ ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ወሳኝ ጉዳይ ቢሆንም በቂ ዋስትና ማቅረብ ካለመቻል፥ በአበዳሪ ተቋማት የሚጠየቁ ቅድመ-ሁኔታዎችን አሟልቶ ካለመገኘት፥ የቁጠባ ባህል ካለመዳበር፥ የፋይናንስ ተቋማት ለብድር የሚያቀርቡት ገንዘብ ውስንነት ያለባቸው ከመሆኑ፥ የሚቀርበው ብድር የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ባህሪ ታሳቢ ያደረገ ካለመሆኑ ወዘተ ጋር ተያይዞ ድጋፉ በበቂ መጠን፥ በወቅቱ እና ምቹ በሆነ መንገድ ለኢንተርፕራይዞች ተደራሽ መሆን አልቻለም። ይህም የዘርፉ ልማት ዕድገትና ውጤታማነት በሚፈለገው ደረጃ እንዳይሆን የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል።

የጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራየዕዞች ልማት እንዲፋጠንና ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ለማስቻል ከሚደረጉ ሌሎች ድጋፎች ባሻገር የፋይናንስ ድጋፍ በተመጣጣኝ ዋጋ፥ ኢኖቬቲቭና አካታች በሆነ መልኩ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ነው። ከዚህ አኳያ የድጋፉን ተደራሽነት ለማስፋት፥ ውጤታማነቱን ለማሻሻልና ለተጠቃሚዎች ምቹ እንዲሆን ለማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ስልቶች እንዲተገበሩ ከሚመለከታቸው ጋር በትብብርና በቅንጅት ይሰራል።

- ኢንተርፕራይዞችን ስለ ፋይናንስ ስራ አመራር፥ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ፥ የንግድ ዕቅድ አዘገጃጀት፥ የብድር ማመልከቻ አቀራረብ፥ የጥሬ ገንዘብ ስራ አመራር/Cash flow management/፥ ዲጂታል ፋይናንስ እንዲሁም ስለ ፋይናንስ አቅርቦት አማራጮች ወዘተ ግንዛቤ እንዲጨብጡና አቅማቸው እንዲገነባ ይደረጋል፤
- በስራ ሂደት የፋይናንስ እጥረት ለገጠመው ኢንተርፕራይዝ ሁሉ መፍትሔው ብድር ማመቻቸት ላይሆን ይችላል። የፋይናንስ እጥረቱ ትክክለኛ ምክንያት በጥናት (diagnosis)

እንዲለይ በማድረግ ችግሩ ሊፈታ የሚችለው ብድር በማመቻቸት እንደሆነ ሲታመንበት ኢንተርፕራይዞች ከፋይናንስ ተቋማት ብድር እንዲያገኙ ይደረጋል፤

- በተራዘመ ጊዜ የሚመለስና በቂ የእፎይታ ጊዜ ያለው ብድር በዝቅተኛ ወለድ ምጣኔ የሚቀርብበት ስርዓት (Concessional loan) ተግባራዊ ይደረጋል፤
- ፈጠራን የሚያበረታታ የፋይናንስ ድጋፍ (Innovative grant) አሰራር ይዘረጋል፤
- እስከ አሁን ሲተገበሩ የነበሩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ይበልጥ ምቹና ተደራሽ ለማድረግ ከሚሰሩ ስራዎች ጎን ለጎን አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታውን ባገናዘበ ሁኔታ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት ስርዓቶች (ኢንቮይስ ፋክተሪንግ፥ ኢኪዩቲ ፋይናንሲንግ፥ ቬንቸር ካፒታል፥ ክራውድ ፈንዲንግ ወዘተ) እንዲስፋፉ ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
- የባንኮችን መመዘኛ መስፈርቶች አሟልተው በቂ ዋስትና ማቅረብ ባለመቻላቸው ብድር ለማግኘት የሚቸገሩ ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍና የፋይናንስ ተቋማት ለኢንተርፕራይዞች እንዲያበድሩ ለማበረታታት የሚያስችል የብድር ዋስትና ስርዓት (de-risking facility/ credit guarantee scheme) ተግባራዊ ይደረጋል፤ ይህም ተቋማቱ ለብድር የሚያቀርቡት ገንዘብ በማመቻቸት እና ኢንተርፕራይዞች ከጅምሩ ለብድር ዝግጁ እንዲሆኑ በመደገፍ ጭምር የሚፈፀም ነው፤
- ኢንተርፕራይዞች ብድር እንዲያገኙ ብቻ ሳይሆን በወሰዱት ብድር ሰርተውና ውጤታማ ሆነው ብድራቸውን እንዲከፍሉ ማድረግ ቀጣይነት ባለው መልኩ የዘርፉን የፋይናንስ ፍላጎት ለማሟላት የሚረዳ በመሆኑ የብድር አቅርቦቱ ቀጣይነት ካለው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ጋር ተቀናጅቶ እንዲተገበር ይደረጋል፤
- ኢንተርፕራይዞች የዲጂታል ፋይናንሲንግ አማራጮችን (mobile money, agent banking etc.) እንዲጠቀሙ ለማስቻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተከታታይነት ባለው መልኩ በቅንጅት ይሰራል።

### 2.1.1.8. የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የአካባቢና የማህበራዊ ደህንነትን በጠበቀ ሁኔታ ሊፈጸም እንደሚገባ በተለያዩ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎችና መመሪዎች የተመላከተና በሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊተገበር የሚገባው ስለመሆኑ የተጠቀሰ ቢሆንም ከኢንተርፕራይዝ ልማት አኳያ የምንከተለው አቅጣጫም ከዚሁ ጋር የሚናበብ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ይጠበቅብናል።

በዚህ መሰረት የአካባቢ ጥበቃ ደንቦች እና የማህበራዊ ደህንነቶች እንዲከበሩ፡-

- የማምረቻ ቦታዎች ከብክለት የጸዱና በሥነ-ምህዳር፣ በማህበረሰብ እና በሰው ጤና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳይኖራቸው ይሰራል፤
- ኃይል ቆጣቢ የኢንዱስትሪ ልማት፣ የመልሶ መጠቀም አሰራር፣ የብክለት መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን በመጠቀም አረንጓዴ የኢንዱስትሪ ልማት እና ሰርኩላር ኢኮኖሚ ሞዴሎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፤
- በማምረቻ ቦታዎች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማዎችን በማካሄድ ዝቅተኛውን መስፈርት ማሟላታቸውን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፤
- አረንጓዴ የኢንተርፕራይዝ ልማትን የሚደግፉ ማበረታቻዎች እንዲስፋፉና እንዲዘረጉ ይደረጋል፤
- የስራ ቦታዎች ለሰራተኞቻቸው ምቹና ደህንነታቸው የተጠበቀ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፤
- የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቱ አካታች (ወጣት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች ወዘተ) እንዲሆን ይደረጋል፤

## 2.2. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ስልቶች

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን መረጃ በማደራጀትና በመተንተን፤ ክፍተትን መሰረት ባደረገ መልኩ የሚፈፀም ሲሆን በመሰረታዊነት በኢንተርፕራይዝ ደረጃ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ቅንጅታዊ አሰራር በመዘርጋት ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚከናወን ይሆናል።

አገልግሎቱን በመስጠት ሂደት ካለው ሀብት ውስንነት አኳያ ሁሉንም ኢንተርፕራይዞች በተመሳሳይ ጊዜ ተደራሽ ለማድረግ በማይቻልበት ሁኔታ በወጪ ምርት ማምረት የተሰማሩ፣ ተኪ ምርት ለሚያመርቱ፣ በቴክኖሎጂና በፈጠራ ስራ ላይ የተሰማሩ፣ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች በባለቤትነት የሚያስተዳድሯቸው ኢንተርፕራይዞች የአገልግሎቱን ቅድሚያ ያገኛሉ።

### 2.2.1. ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የምርት ጥራትና ምርታማት በማሻሻል በዘላቂነት በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎችን ከራስ አቅምና ቁርጠኝነት በማጣመር ስኬት ማስመዝገብ

ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት በተለይ ሞዴል ኢንተርፕራይዞች የዘመናዊ የአሠራር ስርዓት በመታገዝ ውጤታማ የፈጠራና የቴክኖሎጂ መፍለቂ እንዲሆኑ ይሰራል፡፡ በዚህ መሠረት ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከምንጠቀምባቸው ስልቶች መካከል

- ሞዴል ኢንተርፕራይዞች መፍጠር፣ ማበረካት እና የሞዴል ኢንተርፕራይዞችን ምርጥ ተሞክሮ በመለየትና በመሰነድ ለሌሎች አርዐያ እንዲሆን የውጤታማ ሂደቶችን ማስፋት እንደ ስልት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ይኸውም በአሰራር ስርዓት የምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስፋት የአሠራር ስርዓት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡
- የምርጥ ተሞክሮ ስነዳ ቀላል እና ኢንተርፕራይዞች በቀላሉ ልምድ በመለዋወጥ ተወዳዳሪነታቸውን እንዲያሳድጉ ልምድ ልውውጥ መድረኮች እንዲመቻቹ ይደረጋል፤
- ዓለም አቀፍዊ፣ ቀጠናዊ  እና ሃገራዊ ኤግዚቢሽንና ባዛር እንዲሁም የኢንተርፕራይዝ የደረጃ ዕድገት ሽግግር መርሃ ግብሮች የተቀመሩ ተሞክሮዎች ማስፊያ ስልቶች ሆነው እንዲያገለግሉ ይደረጋል፤
- ብሔራዊና ሃይማኖታዊ በዓላት ጋር በማስተሳሰር በቴክኖሎጂ፣ በፈጠራ ሥራ ለየት ያለ ሥራ ያላቸው ሞዴል ኢንተርፕራይዞች  የተቀመሩ ተሞክሮዎች በድረ-ገጽ፣ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን እና መሠል አማራጮች እንዲሰፉ በማድረግ ልምድ እንዲያገኙ ትምህርት እንዲወስዱ ከተቋማዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

### 2.2.2. ክላስተር መሰረት ያደረገ ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት

ክላስተርን መሰረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ በአንድ አከባቢ ተሰባስበው ብዛት ያላቸውና ተመጋጋቢ የሆኑ የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርቱና አገልግሎት የሚያቀረቡ ተመሳሳይ ስጋትና መልካም አጋጣሚዎች የሚጋሩ ኢንተርፕራይዞችን ተደራሽ ለማድረግ ክላስተርን መሰረት ያደረገ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ ስልት ይከተላል፡፡ ኢንተርፕራይዞች በክላስተር በማደራጀት የሚሰጠው የኢንዱስተሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ሊያገኙ የሚያስችል ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይህ ስልት ድጋፎችን በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ፤ የተሳለጠ የግብዓት አቅርቦት፣የክህሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ገበያ ትስስርን የሚያጠናክር በመሆኑ ለኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አሰጣጥ ውጤታማነት ወሳኝ ነው፡፡

- የግብአት፣ፋይናንስ፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታና አቅርቦትና መሰል የኢንተርፕራይዞች ፍላጎቶችን በተቀናጀ፣ወጪ ቆጣቢና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ ምላሽ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

- የክላስተር ልማትና አስተዳደር የኢንተርፕራይዞችና ባለድርሻ አካላት የኢኮኖሚ-ማህበራዊ ትስስር( networking) እንዲጎለብት ይደረጋል
- በውስን ባለሙያዎች አገልግሎቱን ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል
- በኢንተርፕራይዝ አቅም በላይ ሆነ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ቴክኖሎጂና ማሽነሪ፤ እና ሌሎች የጋራ መገልገያዎችን አገልግሎት እንዲያገኙ እንዲቋቋሙ ይደረጋል፤ ያሉትን በማዘመን ኢንተርፕራይዞች ቴክኖሎጂ አገልግሎት እንዲገኙ ይደረጋል
- በእሴት ሰንሰለት መሰረት የኊልዮሽና የፊትዮሽ፤ የጎንዮሽና የአቀበታዊ ትስስርን ታሳቢ ያደረገ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ይሰጣል
- ነባራዊ እውነታ (AS-IS) ከሌላ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር የተሻለ ተሞክሮ (Benchmark) በማነጻጸርና በተሟላ መልኩ ክፍተት የሚያሳይ እንዲሆን ይደረጋል

### 2.2.3. የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር፣

ከፍተኛ ትምህርት፣ቴክኒክና ሙያ ተቋማት እና የምርምር ተቋማት ከኢንዱስትሪ ጋር በመተሳሰር ምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግርና የማማከር አገልግሎት ሥራዎችን ማከናወን ስለሚጠበቅባቸው እና ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪ ለመገንባት ለኢንዱስትሪው ብቁ የሰው ኃይል፣ ችግር-ፈቺ ምርምር የማካሄድና ቴክኖሎጂ የማመንጨት ተልዕኮ ይኖራቸዋል፣

የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር በጋራ ተጠቃሚነትና የትስስር አካላትን ንቁ ተሳታፊነት ስለሚጠይቅ እንዲሁም በሀገራችን ብሔራዊ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፤

ኢንርፕራይዞች ምርታቸውንና አገልግሎታቸውን በጥራት ለገበያ ማቅረብ እንዲችሉ ሥራዎቻቸው በጥናትና ምርምር እንዲሁም በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ይደረጋል፤

ፈጠራ እና የእምሮዊ ንብረት መብት ትኩረት ተሰጥቶ

ዲጅታል ትራንስፎርሜሽን ቁልፍ የቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ማስፋፍያ ስልት ሆኖ እንዲያገለግል ይደረጋል፤

### 2.2.4. ዲጅታላይዜሽን

ለኢንተርፕራይዞች በስራ ቦታቸው እና በስልጠና መስጫ ማዕከላት ከሚሰጡ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ባሻገር  ዌብ ፖርታል፣ የሞባይል መተግበሪያ/የፅሁፍ መልዕክት፤ የጥሪ ማዕከል፤ የተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች (ዋትስአፕ እና ቴሌግራም ግሩፕ፥ ፌስቡክ ወዘተ) የመሳሰሉትን  ዲጅታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አገልግሎቱ ተደራሽ ይሆናል፡፡

### 2.2.5. ኢንተርፕራይዝ ተኮር ኤክስቴሽን አገልገሎት

ይህ አገልግሎት በተናጠል በኢንተርፕራይዞች የማምረቻ ቦታ መገኘት የሚጠይቁና በስራ ቦታቸው ላይ በመተግበር መደገፍ የሚፈልጉ አገልግሎቶችን (ለአብነት የማሽን ተከላ፣ ኮሚሽኒንግና ጥገና፣ የማምረት አቅም ልኬት፣ ካይዘን ወዘተ) የምንሰጥበት መንገድ ነው፡፡

## 2.3. የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የአፈጻጸም ቅደም ተከተል

1. የተጠቃሚዎችና ባለድርሻ  አካላትን መረጃ ማደራጀት
2. አገልገሎትን ማስተዋወቅ
3. የአገልግሎት ጥያቄ መቀበል
4. የአገልግሎት ውል ስምምነት መፈራረም፤
5. የነባራዊ ሁኔታ ግምገማ/ትንተና (Situational analysis) ማካሄድ፡- ለጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ከመሰጠቱ አስቀድሞ ኢንተርፕራይዙ ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ፥ ችግሮቹንና መፍትሔዎቹን ለመለየት ይቻል ዘንድ በመሰረታዊነት የሚከተሉትን መረጃዎች ያካተተ የነባራዊ ሁኔታ ትንተና መስራት ያስፈልጋል፡፡
    - የኢንተርፕራይዙ ስም፥ የባለቤትነት ሁኔታ (Ownership type)፥ የተሰማራበት የስራ መስክ፥ አድራሻ፥ የተቋቋመበት ዓ/ም፥ ያለው ቋሚ ሰራተኛ ብዛት፤


- ዋና የምርት ዓይነት፣ የማምረት አቅም በቀን/በወር፣ የአቅም አጠቃቀም በ%፣ ዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎች፣ የጥሬ ዕቃ ምንጭ፣ የሚጠቀመው ቴክኖሎጂ/መሳሪያና ያለበት ሁኔታ፣ የጥራት ቁጥጥር ልምድ፣ ብክነትን ለመቀነስ የሚከተለው አሰራር፣ የስራ ላይ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚተገበሩ አሰራሮች፤
- የንግድ ስራ አመራር፣ የንግድ ዕቅድ፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣
- የሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣ የዋጋ ትመና ስትራቴጂ፣ የሽያጭ መንገዶች፣ የገበያ ሽፋን፣ ዋና ደንበኞች፣ የሽያጭ መጠን አዝማሚያ፣ የግብይት ስልቶች፤
- የዕሴት ሰንሰለት ትንተና ማጠቃለያ/ ከግብዓት አቅራቢዎች እና ከገዥዎች ጋር ያለው ትስስር፣ ከመንግስት ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነትና ያገኘው ድጋፍ፣ በኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ስለመሳተፉ፤
- አዳዲስ የአመራረትና የአሰራር ቴክኒክ መጠቀም፣
- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ለስራው ስለመጠቀሙ፣
- ወርሃዊ ወጪ/ ነጠላ ወጪ ዝርዝር
- በኢንተርፕራይዙ የተለዩ ችግሮችና መፍትሔዎች

6. የተለዩ ችግሮች የሚፈታውን አካል መለየት
    - የተለዩ ችግሮችን ለሚፈታው ባለድርሻ አካል ማሳወቅ
    - ውይይት በማደርግ ስምምነት ማድረግ
7. የድርጊት መርሐ-ግብር ማዘጋጀትና የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ
    - የኢንተርፕራይዙ ስም፣ የተሰማራበት የስራ መስክ
    - የተለዩ ችግሮች (በማምረት፣ በክህሎት/ዕውቀት፣ በገበያ፣ በፋይናንስ ስራ አመራር፣ በቴክኖሎጂ፣ በጥራትና የምርት ደረጃ፣ ወዘተ)
    - ችግሩን ለመፍታት በኢንተርፕራይዙ የሚከናወኑ ስራዎች (ተግባር፣ ወጪ፣ ጊዜ)
    - በኤክስቴንሽን ባለሙያ የሚሰጡ/የሚመቻቹ ድጋፎች (ተግባር፣ ወጪ፣ ጊዜ)
8. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፤እንዲሰጥ ማድረግ፤
    - ቀድመው ለተለዩና ስምምነት ላይ ለተደረሰባቸው ችግሮች
    - አገልግሎት በመስጠት ሂደት በጋራ ለተለዩ ችግሮች
9. የአገልግሎቱን ሪፖርት ማቅረብ

- ችግሩን ለመፍታት በኢንተርፕራይዙ የተወሰደ እርምጃና የተገኘ ውጤት
- በባለሙያው የተሰጡ/የተመቻቹ ድጋፎችና የተገኘ ውጤት
- መፍትሔ ያላገኙና ቀጣይ ድጋፍና ክትትል/ መፍትሔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች

10. ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት
11. ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ

**ፍሰት ማሳያ**



## ክፍል ሶስት

## 3. የአስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ተግባራዊ ለማድርግ የተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት

### 3.1 የአስፈፃሚና ፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

#### 3.1.1. ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማትንና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት እንዲሰጥ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ለተጠሪ ተቋማት፣ ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በተዋረድ፣ ሌሎች ሚና ያላቸውን ተቋማት አቅም ይገነባል፣ በቅንጅት ይሠራል
- ከኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ጋር በተያያዘ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር ይለያል፣ ይቀምራል፣ እንዲሰፉ ያደርጋል፤
- ለውጤታማ ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ለመሰጠት ከፌደራልና የክልል አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣ ለዘርፉ አሳታፊና ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ ስለሚመጣበት ሁኔታ ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤
- ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን የሚሰጠው የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ውጤታማ እንዲሆኑ የማትጊያ ስልት ይቀይሳል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

#### 3.1.2. የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

- የኢንተርፕራይዝ ልማቱን የሚደግፉ የድጋፍ ማዕቀፎችን፣ የአሰራር ስርዓቶችን እና እቅዶችን ያዘጋጃል፤ ይተገብራል፤ ተግባራዊ እንዲሆኑም ያስተባብራል፤
- የኢንተርፕራይዞችን ልማትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችል ውጤታማ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሠጣል፣ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፤

- በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን  አገልግሎት አሰጣጡ ላይ የክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በተዋረድ፣ ሌሎች ሚና ያላቸውን ተቋማት አቅም ይገነባል፣ በቅንጅት ይሠራል
- ከኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን  አገልግሎት  ጋር በተያያዘ ኢንተርፕራይዝ ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር ይለያል፣ ይቀምራል፣ እንዲሰፉ ያደርጋል፤
- ከክልሎች፣ ከከተማ አስተዳደር ቢሮዎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት  የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን  አገልግሎት ስራዎችን ያቅዳል፣ ይተግብራል፣ የአሰራር ስርዓትን ይዘረጋል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል
- ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን  አገልግሎት የአሰራር ስርዓት ሰነዶችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያዘጋጃል፤ አገልግሎቱን ለሚሰጡ ሙያተኞችና አመራሮች ተደራሽ በማድረግ ግንዛቤ ይፈጥራል
- በዩኒቨርሲቲዎችና ምርርምር ተቋማት የሚሰሩ ቴክኖሎጂዎችን በጋራ በመሆን ኢንተርፕራይዞች እንዲደርሱ እና በትስስር እዲሰሩ ድጋፍ ያደርጋል
- ለኢንተርፕራይዞች በተለይም ገቢ ምርቶችን ለሚተኩ እና ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነትና ውጤታማነት ማነቆ የሆኑ ጉዳዮች በጥናት እንዲለዩና መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
- ለኢንተርፕራይዞች አስፈላጊ የሆኑ የሥልጠና፣የጥናት፣ የፋይናስ፣ የማምረቻ መሣሪያ፣ የቴክኖሎጂ፣ የምክር አገልግሎት፣ የማምረቻ ቦታና መሠረተ-ልማት፣ የግብዓት፣ የገበያ ትስስርና ሌሎች ድጋፎች በክፍተትና በዕድገት ደረጃ ላይ ተመስርተው እንዲቀርቡ ያደርጋል፤ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፤
- ለኢንተርፕራይዝ አገልግሎት የሚውሉ መሠረተ-ልማት የተሟላላቸው የማምረቻ፣ ማሳያና መሸጫ ማዕከላት ያለማል፣ ያስተዳድራል፤

### 3.1.3. የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር

- ለጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጠዉን የኤክስቴንሽን አገልግሎትንና የአንድ መስኮች አገልግሎትን ይሰጣል፤ያሰተባብራል
- በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት የሚዘጋጁ የሥርዓተ-ሥልጠና ካሪኩለሞች የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ፍላጎት መሰረት ያደረገ እንዲሆን ያደርጋል

- የሰው ኃይል ልማትን ለማፋጠንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ውጤታማነት ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ያቋቁማል፣ ይመራል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- በቴክኒክን ሙያ ስልጠና የሚሰሩ የፈጠራ ስራዎችን እና ቴክኖሎጆችን የኢንተርፕራይዞች ፍለጎት መሰረት ያደረገ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ማእከል አቅማቸው እንዲገነባ ያደርጋል፤
- ለኢንተርፕራይዞች አንቀሳቃሾች የሙያ ብቃት እንዲያገኙ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያበቃ በድርጅት/በስራ ቦታቸው ውስጥ ሥልጠናዎችን በማዘጋጀት ይሰጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል

### 3.1.4. የክልልና ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ባለድርሻ አካለት ተግባርና ኃላፊነት

የጥቃቅን፣አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዘርፍ አስፈፃሚና ባለድርሻ አከላት የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ለኢንተርፕራይዞች ከመስጠት አኳያ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

- የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ሁለንተናዊ አቅም ለማሳደግ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣሉ፣
- የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች አቅም ይገነባሉ
- በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ለሚሰማሩ ጥቃቅን፣ አነስተኛ፣መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የኢንዱስትሪ መንደሮችን፣የክላስተር ማእከላትንና ለነዚሁ የሚያስፈልገው መሬት ከሶስተኛ ወገኖች ይዞታ ነጻ እንዲሆን ይሰራል፣የቦታ ካርታና ፕላን በማሰራትም ሆነ እስከየ መዳረሻቸው የሚዘልቅ መሠረተ-ልማት እንዲሟላላቸው በማድረግ ያስተላልፋል፤
- ጥቃቅን፣አነስተኛ፣መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ተስማሚ ቴክኖሎጅዎችና አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ የዘርፉ የመወዳደር አቅም እንዲጎለብት ይሠራል፤
- የጥቃቅን፣አነስተኛና የመካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት የሚረዱ ምርጥ ተሞክሮዎችን ያሰባስባሉ፣ ይቀምራሉ፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫሉ፤

- የአምራች ኢንተርፕራይዞችን ከግብዓት አቅርቢዎችን እና ከግብዓት አምራች ኢንተርፕራይዞች ትስስር መፍጠር
- የማኑፋክቸሪንግ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ ላይ ለተሰማሩ ኢንተርኘራይዞች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ምርታቸውን ለውጭ ሀገር እንዲያቀርቡ ያግዛሉ፡ ፡
- የአምራች ኢንደስትሪዎችን የገበያ ችግር ለመቅረፍ ከተለያዩ አካላት ጋር የገበያ ትስስር እንዲፍጠርላቸው ያደርጋሉ፤ ኤግዘቢሽንና ባዛሮች እንዲዘጋጅ ያደርጋሉ፣ በውጭ ሀገር በሚካሄደ ኤግዘቢሽንና ባዛሮችን እንዲሳተፈ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ፤
- ለአምራች ኢንደስትሪዎች የተሰማሩበትን የሥራ ዘርፍ በአግባቡ ማካሄድ የሚያስችላቸውን የብድር የካፒታል ሊዝና ፋይናንስ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋሉ
- ተኪ ምርት የሚያመርቱና ኤክስፖርት የሚያያርጉ አምራች ኢንዱስትሪዎች የገበያ ድርሻ እና ምርታማነት እንዲያድግ የድጋፍና ክትት ስርዓት ይዘረጋሉ፣ ተግባራዊ ያደርጋሉ ፣ ውጤታማነቱን ይከታተላሉ።

## 3.2. የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት መንግስት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማምጣት የሚያስችሉ የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን አውጥቶ በመተግበር ላይ ይገኛል። በዚህ መሠረት ቀጥተኛ ከኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ አኳያ የባለድርሻ አካላት ሥልጣንና ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.2.1. የግብርና ሚኒስቴር

- ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብት የቴክኒክ ድጋፎችን በመስጠት የማኑፋክችሪንግ ዘርፈ የግብአት ፍላጎትን ትስስር እንዲፈጠር ማድረግ፣
- ለኢንዱስትሪው የሚቀርቡ የሰብል ምርት፣ እንስሳትና ዓሳ ምርትና ተዋጽኦ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት
- ከተቋማት ጋር በጋራ በመሆን እምቅ አቅሞችን መለየት

- የሰብል፣ የእንስሳትና የዓሳ ምርት ምርታማነትን በማሳደግ፣ ለኢንዱስትሪው በቂ ግብዓት እንዲቀርብ በማድረግ የምርት ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ
- የቡናና የሻይ ልማት  የግብይት ሥራዎች  የእሴት ጭማሪን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ለማኑፋክቸሪንግ ዘረፉ ትኩረት ሰጥቶ ማስተባበር

### 3.2.2. የማዕድን ሚኒስቴር

- የኮንስትራክሽን ግብዓት አምራች ኢንዱስትሪዎችን ከማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ጋር የግብዓት ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፤
- የማዕድን ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ልማት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- በባህላዊ መንገድ የሚመረቱ ማዕድናት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል ውጤታማና ቀልጣፋ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤
- የማዕድንና የሥነ-ምድር መረጃዎች ማደራጀትን ሥራን ያስተባብራ፣ መረጃዎችን ለኢንተርፕራይዞች ተደራሽ ያደርጋል፤

### 3.2.3. የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

- የሀገር ውስጥ ኢንተርፕራፕራዝ    ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የሀገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን ያስተባብራል፤
- ኢንተርፕራይዞች የሚያመርታቸውን ምርቶች ደረጃ እንዲወጣላቸው ድጋፍ ያደርጋል፤
- ኢንተርፕራይዞች ምርቶችን የጥራት ብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤
- አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣በሌሎች አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ

ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

### 3.2.4. የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

- በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማትና ባለሙያዎች አቅም ግንባታን ይደግፋል፤ የሙያ ማህበራትንና የጥናትና ምርምር ተቋማትን ይደግፋል፣ ያበረታታል፤
- የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለመዳሰስ፣ ተገቢ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግና በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- ከኢንተርፕራይዞች በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ ይመዘግባል፣ የማጠቃለልና የማቀብ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ለቀጣይ ሥራ እንዲውሉ ያደርጋል፤
- የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት በቴክኖሎጂ የተደገፈና ቀልጣፋ እንዲሆን ይሰራል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤
- የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ መረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃዎችን ያጠናቅራል፤ ለኢንተርፕራይዞች ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፤

### 3.2.5. የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር

- ሀገራዊ የተቀናጀ የመሠረተ ልማት፣ መዋቅራዊ እና ማስተር ፕላን በሚዘጋጅበት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች/ኢንተርፕራይዞች ታሳቢ ይደረጋሉ፤
- በሀገር አቀፍ ደረጃ የከተሞች መዋቅራዊና መሠረታዊ ማስተር ፕላን ዝግጅትን ወቅት ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ልዩ ትኩረት እንዲታይ ያደርጋል፡፡
- በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ምርምር ያካሂዳል፤ የሀገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ግብዓት መጠቀምን ያበረታታል፤
- በሚዘጋጁ ማስተር ፕላን የኢንዱስትሪ መንደሮች እና ክላስተር ማእከላት እንዲካተቱ ያደርጋል፤
- ኢንዱስትሪ መንደሮችን የመንገድ መሠረተ ልማት ሥራዎች ተደራሽ ባደረገ መልኩ እንዲሆኑ ድጋፍ ያደርጋል፤

### 3.2.6. የትምህርት ሚኒስቴር

- በከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪው/ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የእርስበርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ በጋራ የሚያካሄዱ የትስስር ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
- በዩንቨርስቲ -ኢንዱስትሪ ትስስር የጋራ መገልገያ ፋስልቲሽን ላብራቶሪ፣ወርክሾፕ እና ምርምር ማእከላት የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- ትስስሩን ሊያጠናክር የሚችል፣ ሀብት የሚመነጭበትና በትስሰር አካላት ለሚከናወኑ ተግባራት የሚውልበት የትስስር ፈንድ አሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከምክር ቤቱ ጋር በመሆን ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል።

### 3.2.7. የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን

- ገቢና ወጪ ዕቃዎችን በተመለከተ መረጃዎችን ይይዛል፣ ያደራጃል፣ ያጠናቅራል፣ ለኢንተርፕራይዞች ፣ለሚመለከተው አካላት ያሠራጫል፤
- በመስኩ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን መሰረት በማድረግ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፣ የቀረጥ ነፃ መብቶችንና ማበረታቻዎችን ኢንተርፕራይዞች እንዲያገኙ ድጋፍእና ክትትል ያደርጋል፤
- በጉምሩክ ህጎች መሰረት ልዩ ልዩ ፈቃዶችን ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤

### 3.2.8. የኢትዮጵ ኢንዱስትሪ ግብአት ልማት ድርጅት

- ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በአገር ውስጥ ባለው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና የግብርና ሥራዎች መካከል ጥብቅ ቁርኝት እንዲኖሩ በማደረግ አስተማማኝ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት እንዲኖር ያደርጋል፤

- በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በአገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ግብዓት ሲያጥር ጥሬ ዕቃን ኢምፖርት ያደርጋል ወይም በሀገር ውስጥ በከፊል ፕሮሰስ የሚያደርጉ ፋብሪካዎችን አቋቁሞ ኢንተርፕራይዞች ግብዓት ኢንዲያገኙ ያደርጋል፤
- በማኑፋክቸሪንግ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የማምረት አቅማቸውን በሙሉ እንዲጠቀሙ የሎጀስቲክ ማኔጅመንቱን ቀልጣፋ ለማድረግ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በጅምላ ገዝቶ ያቀርባል፤
- ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ግብዓቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ፤ በሚፈለገው ጊዜ ጥራትና መጠን በማቅረብ እንዲሁም ግብዓት ቀርቦላቸው ደረጃቸውን የጠበቁ ምርቶች የሚያመርቱና የገበያ ችግር ያለባቸውን አምራች ኢንተርፕራይዞች በጋራ በመለየትና በየቅርንጫፎች ግዢ ይፈፅማል፤
- ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ግብዓት ከማቅረብ ጋር በተያያዘ ከግብዓት አምራች አቅራቢዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፤
- ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ጥራታቸውን ጠብቀው የሚመረቱ ምርቶችን ከአገር ውስጥና በውጭ አገር ገበያ ይሸጣል፤ ከገዥዎች ጋር ያገናኛል፤ ቀጣይነት ባለው መልኩ ገበያ በሚያገኙበት ሁኔታ በትብብር ይሰራል፤
- የኢግልድ ቅርንጫፎች ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ግብዓት አቅርቦት ላይ በመተባበርና በመቀናጀት እንዲሰሩ አስፈላጊውን ግንዛቤ ያስጨብጣል፤ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤

### 3.2.9. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

- ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሀይል መቆራረጥ ሲገጥሟቸው በቋሚነት ጥያቄዎችን የሚቀበሉ ባለሙያዎች፣ ልዩ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች መስኮት እና ልዩ የስልክ መስመር ያዘጋጃል፤
- ኤሌክትሪክ አገልግሎቱ ከማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ለሚቀርብ ጥያቄ 24 ሰአት አገልግሎት የሚሰጥ ልዩ የጥገና ቡድን ሊመድብ ይችላል፤
- በኢኮኖሚው ላይ ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ የሆኑ ምርቶችን የሚያመርቱ ኢንተርፕራይዞች በመለየት ኢንተርፕራይዞቹ ልዩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

- አስቸኳይ እና ጊዜ የማይሰጡ የሀይል አቅርቦት ጥያቄዎች ሲቀርቡ አምራቾች በራሳቸው በአገልግሎቱ ዲዛይን እና ስፔስፊኬሽን መሰረት ሲፈቀድላቸው አግባብነት ባላቸው የአገልግሎቱ ደንበኞች የኔትወርክ ግንባታ መሰረት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ገዝተው የአገልግሎቱን መስፈርት በሚያሟሉ ኤሌክትሮ ሜካኒካል ኮንትራክተሮች የግንባታ ስራ እንዲሰሩ ያደርጋል፣ የግንባታ ሂደቱን ይከታተላል፤ ግንባታው ሲጠናቀቅም ሀይል የማገናኛት ስራ ይሰራል፤
- ከማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርብለትን ከሀይል አቅርቦት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥበትን እና ጥያቄው የሚስተናገድበትን አግባብ፣ እንዲሟሉ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች እና ስራው ሊፈጅ የሚችለውን ጊዜ በተመለከተ ዝርዝር መስፈርቶችን ያዘጋጃል፤ ያስተዋዉቃል፣፤በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤
- የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ተጠቃሚ የሆኑ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፤

### 3.2.10. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

- ለዘርፉ ልማት የሚውል ፈንድ በመመደብ/እንዲመደብ በማድረግ በረዥም ጊዜና በዝቅተኛ ወለድ የሚቀርብ ብድር እንዲመቻች ማድረግ፤
- በፋይናንስ ተቋማት ከሚሰራጨው ብድር ውስጥ ለጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርበው ብድር ድርሻ እንዲጨምር መስራት፤ የመጣውን ለውጥ መከታተል፥ መገምገምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ፤
- ጥቃቅን፥ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ኢኖቬቲቭ የፋይናንስ ፕሮዳክቶች/አገልግሎቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ መስራት፤ ኢንተርፕራይዞች እንዲጠቀሙባቸው ማስተዋወቅና መደገፍ፤
- የብድር ዋስትና ስርዓት እንዲዘረጋና ወደ ስራ እንዲገባ ማድረግ፤
- የኢንተርፕራይዞች አመራሮችና ሰራተኞች ስለ ፋይናንስ ያላቸውን ግንዛቤ (financial literacy) እና የቁጠባ ባህል የሚያሳድጉ ስራዎችን ማከናወን፤

### 3.2.11. ባንኮች፣ የብድርና ቁጠባ ተቋማትና የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበራት

- የፋይናንስ ተቋሙ በሚሰጣቸውና ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ ሊያደርጉ በሚችሉ የፋይናንስ አገልግሎቶች (products/services) ላይ ግንዛቤ መፍጠር፣ ማሻሻያ የሚፈልጉ ካሉም ይበልጥ ምቹና ቀላል እንዲሆኑ መስራት፤
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የዋስትና ችግር የሚያቃልሉ አሰራሮችን በመዘርጋት የአጭር፥ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የስራ ማስኬጃ ብድር በአነስተኛ/ተመጣጣኝ ወለድ ማቅረብ፤
- ከወለድ ነፃ የብድር አገልግሎት መስጠት፤
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ የማምረቻ መሳሪያዎችን እና መገልገያዎችን በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አሰራሩ ማቅረብ፤
- ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በረዥም ጊዜ የሚከፍሉትና ለቋሚ ንብረት (ለአብነት፦ ለማምረቻ፥ መሸጫ ወዘተ) መገንቢያ የሚውል ብድር (asset finance facility) ማቅረብ፤
- ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ለሚፈፅሟቸው የውል ስምምነቶች የሚጠየቁ ዋስትናዎችን **(bonds and guarantees) መስጠት፤**

    - ለስራ ለሚከፈላቸው **ቅድመ-ክፍያ ዋስትና** (advance payment guarantee) መስጠት፣
    - ስራውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት አጠናቀው እንደሚያስረክቡ አስቀድሞ የሚጠየቅ መተማመኛ (performance guarantee) መስጠት፣
    - ስራውን በተቀመጠው በጀት ሰርተው ለማስረከብ የሚጠየቁትን የጨረታ ማስከበሪያ ቦንድ (bid/tender bond) በመስጠት፣
    - አቅራቢዎች ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ለሚፈፅሙት ሽያጭ በስራ ውሉ መሰረት ሙሉ ክፍያው እንደሚከፈላቸው መተማመኛ ደብባቤ (supply guarantee) መስጠት፣
    - የግብዓት አቅራቢዎች ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በዱቤ ግብዓት ማቅረብ የሚችሉበትና ከምርት ሽያጭ በኂላ ክፍያ የሚፈፀምበት የዱቤ ሽያጭ ዋስትና (credit sales guarantee) መስጠት፣

- ኢንተርፕራይዞች ከውጭ ለሚያስገባቸው ማሽኖች/ግብዓቶች በጉምሩክ የሚፈለግባቸውን ክፍያ እንደሚከፍሉ የዋስትና ደብዳቤ (letter of guarantee for payment of customs duty) መፃፍ፣

- የውጭ ምንዛሪ ማመቻቸት፤
- ከውጭ ለሚያስገቧቸው ዕቃዎች ለሚያቀርብላቸው አካል ክፍያው እንደሚከፈለው መተማመኛ (Letters of Credit) አገልግሎት መስጠት፤
- ምርት አቅርበው ወይም አገልግሎት ሰጥተው ካቀረቡለት ድርጅት የሚከፈላቸው ክፍያ እንዳላቸው የሚያረጋግጥ ኢንቮይስ የሚያቀርቡ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ክፍያ እስከሚያገኙ የሚገጥማቸውን የጥሬ ገንዘብ እጥረት የሚያሟሉበት የብድር ስርዓት (invoice discounting finance facility) በመዘርጋት ተጠቃሚ ማድረግ፤
- አምራች ኢንተርፕራይዞች ስለ ንግድ ስራ አመራር፣ የፋይናንስ ስራ አመራር፥ ቁጠባ ወዘተ ያላቸው ግንዛቤ ውስን ስለሆነ የማማከር እና ስልጠና ድጋፍ (non-financial services) በመስጠት መደገፍ፤
- ዲስትሪክቶች/ቅርንጫፎች በአቅራቢያቸው የዘርፉን ልማት ከሚመሩ ቢሮዎች ጋር በግንዛቤ ፈጠራ፣ በተበዳሪ ምልመላ፣ ብድር በማሰራጨት፣ ውጤታማ እንዲሆኑ በመደገፍ፣ ብድር በማስመለስ ረገድ የጋራ እቅድ በማዘጋጀት በቅንጅት እና በትብብር የሚሰሩበትን፣ የተሰሩ ስራዎችን መረጃ/ ሪፖርት ልውውጥ የሚኖርበትን ሁኔታ መፍጠር፣

## ክፍል አራት

## 4. የተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ

### 4.1.የተጠቀሚዎች መብት

- መረጃና ምክር አገልግሎት የማግኘት
- የአቅም ግንባታ ስልጠና የማግኘት
- የአካባቢ ፀጋና የገበያ መረጃ የማግኘት
- የኢንዱስትሪ የግብዓት፣የሰው ኃይል የቴክኖሎጂ ትስስር ድጋፍ ማግኘት
- የፋይናስና የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ማግኘት
- የመሰረተ ልማት አገልግሎት
- የማምረቻ፣ የመሸጫ እና የማሳያ ቦታ የማግኘት
- የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ማግኘት
- የምርት ጥራት ሰርተፊኬሽን
- የምርት ደረጃ የወጣላቸው ምርቶች መረጃ ማግኘት
- የራሳቸው ምርቶች ደረጃ እንዲወጣላቸው
- ቴክኖሎጂ፤ የጋራ መገልገያ ፋሲሊቲዎችን በጋራ የመጠቀም
- ምርታማነት ለማሳደግ ካይዘን፣ ሊን ማኑፋክቸሪንግ፣ባዮና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ድጋፍ የማግኘት
- አዳዲስ የምርት ናሙናዎችን የማግኘት
- የቢዝነስ ፕላንና ፕሮጀክት ፕሮፋይል፣ የማግኘት
- የማሽን ስፔስፍኬሽን፣ የማሽን ተከላና ኮሚሽኒንግና ጥገና አገልግሎት

### 4.2. በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከተጠቃሚዎች የሚጠበቁ ግዴታዎች

- በንግድ ህጉ መሰረት ተመዝግቦ ህጋዊ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያደርግ፣
- ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ መስጠት
- በሙሉ ፍላጎት ብቻ ተመስርቶ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን፣

- የሚሰጠውን ድጋፍ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል በምርት ጥራትና ተወዳደሪነት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት
- ከኢንደስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አቅራቢና በተጠቃሚው ኢንተርፕራዝ የጋራ የድርጊት መርሀ-ግብር እና የውል ስምምነት መሠረት የድርሻውን መወጣት፣
- ምርትና ምርታማነት የሚያሻሽሉ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመጠቀም ዝግጁ የሆነ
- ከሌሎች ኢንዱስትሪዎችና አስፈፃሚ ተቋማትና ባለድርሻ አከላት ጋር በቅንጅት መስራት
- ማህበራዊ ሀላፊነቱን መወጣትና የአካባቢ ጥበቃ ህጎችን ማክበር
- የስራ ላይ ደህንነት፣አካታችነት፣ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ አካላትን (ሴቶች፣ወጣቶች፣አካል ጉዳተኞች፣ህፃናት) መብት ጥበቃን ማረጋገጥ

## ክፍል አምስት

### 5. መረጃ፣ ክትትል፣ ድጋፍና ግብረ መልስ

#### 5.1. መረጃ አያያዝ

በየደረጃው የሚገኙ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጭ አካላት የተጠናከረ እና ወቅታዊ መረጃዎች በመያዝ ለሚመለከተው አካል ማድረስ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመረጃው የሚካተቱ ዝርዝር ተግባራት

- ኢንተርፕራይዞች የተሰማሩበትን የሥራ መስክ፣ የአባላትን የትምህርት ደረጃ፣ ጾታ፣ ዕድሜ ወዘተ መረጃዎች ማሰባሰብና ማጠናቀር፤
- አግልግሎት ያገኙ ኢንተርፕራይዞችን ዝርዝር መረጃ በተሰጠው የአገልግሎት አይነት ለይቶ ማስቀመጥ፤
- በተሰጠው አገልግሎት የተገኘ ውጤት በዝርዝር በየንዑስ ዘርፉ ማደራጀትና ለሚመለከተው ማድረስ፤
- ወቅታዊ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ዝርዝር መረጃዎችን በተደራጀ ዳታ ቤዝ ውስጥ ማስገባት፤

#### 5.2. ክትትል፣ ድጋፍ እና ግብረ መልስ

- በየደረጃው የኢንተርፕራይዞችን ልማት የሚመሩ መዋቅሮች እና የሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ዓመታዊ የጋራ ዕቅድ ያዘጋጃሉ፤
- በዕቅድ አፈፃፀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፤ በየወሩ አፈጻጸሙን በመገምገም ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባሉ፤
- አስቀድሞ በሚዘጋጅና በፈፃሚ አካላት እንዲታወቅ በሚደረግ ቼክሊስት መሰረት በዓመት 2 ጊዜ የመስክ ግምገማዎችን በማካሄድ የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት እንዲቀርብ ይደረጋል፤

- በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙ አስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት በአፈጻጸምና በክትትልና ድጋፍ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት በየሩብ ዓመቱ ግምገማ ያደርጋሉ፤ ውጤታማነቱን ለማሻሻል የሚረዱ የጋራ ውሳኔዎችንና አቅጣጫዎችን ያስቀምጣሉ፤

- የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ውጤታማነትን ለማሻሻል ይረዳ ዘንድ የኢንተርፕራይዞች እና የባለሙያዎች የእርካታ ደረጃ እንዲለካ ይደረጋል፤

- የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎትን በተቀናጀና ውጤታማ በሆነ መንገድ ከመፈጸምና ከመምራት አንጻር በተደረጉ ክትትልና ግምገማዎች መሰረት አፈጻጸሙን ለማሻሻል የሚያስችል ግብረ-መልስ ይሠጣል፤

- ከእቅድ ዝግጅት እስከ ትግበራ ሂደት ያለውን የተቋማት ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አፈፃፀምና ፋይዳ ለማሳየት የሚረዳ ጥናት እንዲካሄድ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፤

### 5.3. የአፈጻጸም መለኪያዎች (Key Performance Indicators)

ዋና ዋና መስፈርት፣ መለኪያ መንገድ እና መግለጫዎቹ እንደሚከተለው ቀርቧል

| ተ.ቁ | የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የውጤት አመላካች | | 2018 ዓ.ም |
|---|---|---|---|
| 1 | ቅንጅታዊ አሰራር | ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የተዘጋጀ የጋራ ስምምነት ሰነድ በቁጥር | |
| | | ከኢንተርፕራይዞች ጋር በቅንጅት ለመስራት የተዘጋጀ የጋራ ስምምነት ሰነድ በቁጥር | |
| | | ከግል ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አቅራቢ ጋራ የተደረገ ስምምነት | |
| | | የተፈጠረ ኢንዱስትሪ - ዩንቨርስቲ/ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና/ ምርምር ተቋማት ትስስር | |
| 2 | አቅማቸው የተገነባ የኢንዱስሪት ኤክስቴሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ባለሙዎች | | |
| 3 | በስልጠና አቅማቸው የተገነባ ኢንተርኘራይዞች በቁጥር | | |
| 4 | በአካባቢና ማህበራዊ ደህንነትና ኢነርጂ አጠቃቀም ላይ ስልጠና ያገኙ ኢንተርፕራይዞች ባለቤቶችና ሰራተኞች በቁጥር | | |
| 5 | ያደገ የማምረት አቅም አጠቃቀም በመቶኛ | | |
| 6 | አግልግሎቱ በመሰጠቱ በተቋቋሙ እና በተጠናከሩ ኢንተርፕራይዞች የተፈጠረ ስራ እድል | | |
| 7 | በተሰጠ አገልግሎት የደረጃ ሽግግር ያደረጉ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | | |
| 8 | የምርት ደረጃ የተዘጋጀላቸዉ ምርቶች በቁጥር | | |
| 9 | የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙ ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | | |
| 10 | | የወጪ ምርት መጠን በቶን | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የወጪ ምርት መጠንና ገቢ ማሳደግ | የወጪ ምርት ገቢ በዶላር | |
| | | ምርታቸውን ለውጪ ገበያ ያቀረቡ ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | |
| 11 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የተኪ ምርት መጠንና ገቢ ማሳደግ | የተተኩ የኢንተርፕራይዝ ምርቶች መጠን በቶን | |
| | | በተኪ ምርት የዳነ የውጭ ምንዛሬ በዶላር | |
| | | ገቢ ምርት የተኩ ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | |
| 12 | የገበያ ትስስር ማሳደግ | የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸው ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | |
| | | የተፈጠረ የገበያ ትስስር በብር | |
| 13 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻ፣ መሸጫና ማሳያ ማዕከላት ልማትና አስተዳደርን ማሻሻል | መሠረተ ልማት የተሟላላቸው ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | |
| | | ለኢንተርፕራይዞች የቀረበ መሬት በሄክታር | |
| | | የተገነቡ የማምረቻ ማሳያና መሸጫ በቁጥር | |
| | | ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | |
| | | ለኢንተርፕራይዝ የቀረበ ኃይል በኪሎ ዋት | |
| | | በቀረበ የኃይል አቅርቦት ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | |
| 14 | ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የቁጠባና የፋይናንስ አቅርቦትን ማሳደግ፤ | ለኢንተርፕራይዞች የቀረበ የስራ ማስኬጃ ብድር በብር | |
| | | የስራ ማስኬጃ ብድር ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | |
| | | ለኢንተርፕራይዞች የተሰራጨ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ በብር | |
| | | የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | |
| | | በቁጠባ ላይ ግንዛቤ የተፈጠረላቸው የኢንተርፕራይዝ ባለቤቶች በቁጥር | |
| | | ከማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የተሰበሰበ ቁጠባ በብር | |
| 15 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የግብዓት አቅርቦትን ማሳደግ | ለኢንተርፕራይዞች የቀረበ ግብዓት በቶን/ስኩዌር ሬት | |
| | | በቀረበ ግብዓት ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች በቁጥር | |
| 16 | ምርጥ ተሞክሮ በቁጥር | የተቀመረ ተሞክሮ ብዛት በቁጥር | |
| | | የሰፋ ተሞክሮ ብዛት በቁጥር | |
| | | ተጠቃሚ ኢንተፕራይዞች ብዛት | |
| 17 | ቴክኖሎጂ ብዛት | የለሙ ቴክኖሎጂዎች ብዛት | |
| | | የተሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች ብዛት | |
| | | ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተፕራይዞች ብዛት | |
| 18 | በዲጅታል ግብይት ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ብዛት | | |
| 19 | የጋር መገልገልያዎች ያገኙ ኢንተርፕራይዞች ብዛት | | |
| 20 | ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ያገኙ ብዛት | | |
| 21 | የወጣቶች፣የሴቶች እና የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት በብዛት | | |

## 6. አባሪዎች

**የኢንተርፕራይዙ መሰረታዊ መረጃ**

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኢንተርፕራይዙ ስም | | | | | | | | | | | | |
| የተሰማራበት ዘርፍ/ ንኡስ ዘርፍ | | | | | | | | | | | | |
| የኢንተርፕራይዙ ጠቅላላ ሃብት/ የእድገት ደረጃ | | | | | | | | | | | | |
| አድራሻ | ክ/ከተማ | ወረዳ | የቤት ቁጥር | ስ.ቁጥር | ኢ.ሜል | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| ባለቤት | ☐ የግል ☐ የህብረት ስራ የማህበር ☐ አክስዮን ማህበር ☐ ሽርክና ማህበር ☐ | | | | | | | | | | | |
| ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመ□ት ቀን/ወር/ዓ.ም | | | | | | | | | | | | |
| የስራ አስኪያጅ ስም | | | | | | | | | | | | |
| የማምረቻ ቦታ ሁኔታ | ☐ የግል | | | | ☐ የመንግስት | | | | ☐ ኪራይ | | | |
| የመሸጫቻ ቦታ ሁኔታ | ☐ የግል | | | | ☐ የመንግስት | | | | ☐ ኪራይ | | | |
| ሰራተኛ ብዛት | ቋሚ | | | | ጊዜያዊ | | | | አጠቃላይ ድምር | | | |
| | ወ | ሴ | አካል ጉዳተኛ | ድምር | ወ | ሴ | አካል ጉዳተኛ | ድምር | ወ | ሴ | አካል ጉዳተኛ | ድምር |
| | | | | | | | | | | | | |
| የሚያመርተው ምርት ተደራሽነት | ☐ ለሀር ውስጥ ገበያ | | | | | ☐ ለውጭ ሀገር ገበያ | | | | | | |
| ግብአት የሚያገኝበት ሁኔታ | ☐ ከአከባቢው ገበያ | | ☐ ከግብአት አምራች | | | ☐ ከውጭ ገበያ | | | ☐ ከአርሶ አደሩ | | | |
| የትምህርት ዝግጅት በኢንተርፕራይዙ የሚገኙ አባላት በቁጥር | ሶስተኛ ዲግሪ | ሁለተኛ ዲግሪ | የመጀመሪያ ድግሪ | ዲፕሎማ | ሰርተፊኬት | አስራሁለተኛ ክፍል | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| የፋይናንስ አቅርቦት | የስራ ማስኬጃ ወሰወደ የመለሰ | የስራ ማስኬጃ ወሰወደ ያልመለሰ | የስራ ማስኬጃ ወሰወደ በበመለስ ላይ ያለ/ች | የመሳሪያ ሊዝ ተጠቃሚ የሆነ/ች | የመሳሪያ ሊዝ ተጠቃሚ ያልሆነ/ች | የመሳሪያ ሊዝ ለመጠቀም ጥያቂ ያቀረበ/ች | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |

ቅጽ 01

## የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግልት ጥያቄ ማቅረቢያ

ጉዳዩ፡- <u>የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልገሎት እንዲሰጠኝ ስለመጠየቅ፤</u>

እኔ ________________የ ______________________ኢንተርፐራይዝ ባለቤት/ ስራ አስኪያጅ ክፍተትን መሰረት ያደረገ ጥናት በማካሄድ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት እንዲሰጠኝ ስል አመለክታለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

**ቅጽ- 02**

## የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የውል ስምምነት

### 1 ውል ተቀባይ

የ-----------------------------------------------------------------------ተቋም

- የተሰማራበት የስራ መስክ -------------------------------------------------------------------
- አድራሻ፡ ክልል------------------- ዞን -------------------- ወረዳ---------------------- ቀበሌ ------------- ---------- የቤ/ቁጥር --------------------------- ስልክ ቁጥር ---------------------------------

ውል ተቀባይ በውል ሰጪ የቀረበውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ጥያቄ መሰረት በማድረግ እና የውል ሰጪውን የንግድ ሁኔታ ግምገማ /Evaluation / በማዘጋጀት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የድጋፍ መስኮች ለውል ሰጪ የኢንዱስትሪ የኤክስቴሽን አገልግሎት ይሠጣል፡፡

1. -------------------------------------------------
2. -------------------------------------------------
3. -------------------------------------------------

ውል ተቀባይ ለውል ሰጪ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በሚሠጥበት ወቅት የሚያገኛቸውን የንግድና የግል መረጃዎች ሚስጢራዊነት የመጠበቅና ያለውል ሰጪ ፈቃድ ለሌላ ስራ አሳልፎ ያለመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

ውል ሰጪ በውል ተቀባይ መ/ቤት ወይም በተወካዩ አማካይነት የሚሰጠውን የኤክስቴንሽን አገልግሎት በድርጊት መርሐ-ግብር ላይ በተስማማው መሰረት የድርሻውን የመወጣትና ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በውል ተቀባይ ለሚሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት አጠቃላይ ወጪ ውስጥ -------------------- በመቶ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡

| ውል ሰጪ | ውል ተቀባይ |
|---|---|
| ስም -------------------------------------- | ስም ----------------------------- |
| ፊርማ ----------------------- | ፊርማ ----------------------- |
| ቀን -------------------------- | ቀን ---------------------------- |

**ቅጽ-03**

# የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሁኔታ ትንተና

| ተ.ቁ | የኢን□ርፕራይዙ ስም | አድራሻ | | | | | የአደረጃጀት ሁኔታ | የተመሰረተበት ዘመን | አሁናዊ ጠቅላላ ሀብት | የሚያመርተው የምርት ዓይነት | የማምረት አቅም አጠቃቀም | የንግድ ዕቅድ፣ ሂሳብ መዝገብ፣ ድርጅታዊ መዋቅር | የጥሬ እቃ አቅርቦት፣ የገበያ ሁኔታ፣ ዲጅታል ቴክኖሎጂ መጠቀም | በኢንተርፕራይዙ የተለዩ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል/ ከተማ | ዞን/ ክፍለ ከተማ | ወረዳ/ ከተማ | ቀበሌ/ ልዩ ቦታ | □ስራ አስኪያጅ ስልክ | | | | | | | | ችግሮች | መፍትሔዎች |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |

**ቅጽ 04**

# የአገልገሎት መስጫ የድርጊት መርሃ-ግብር

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | አድራሻ | | | | | በኢንተርፕራይዙ የሚታዩ መሰረታዊ ችግሮች እና ዓይነቶች | ችግሩ ያለበት ደረጃ | ችግሩ በማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የሚፈታበት አግባብ | ፈጻሚ አካል | የሚፈታ በት የጊዜ ሰሌዳ | ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል የባለድርሻ አካላት ሚና | የስኬት/ የውጤት አመልካ ች | አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልገው ግብዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል/ ከተማ | ዞን/ ክፍለ ከተማ | ወረዳ/ ከተማ | ቀበሌ/ ልዩ ቦታ | □ስራ አስኪያጅ ስልክ | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |

ቅጽ- 05

# ዕለታዊ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ፕሮግራም መከታተያ ቅጽ

ዕለት----------------- ቀን -----------ወር ----------------- 201-------ዓ.ም

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሰጪ ባለሙያ

ስም ---------------------------------------------------

ፊርማ --------------------------------------------

| ተቁ | የምክር አገልግሎት የሚያገኙ ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር | የድርጅቱ አድራሻ | | | የምክር አገልግሎት የሚሰጥባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች | የምክር አገልግሎት የሚሰጥባቸው ሰዓት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቀበሌ | የቤት ቁጥር | ስልክ ቁጥር | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

የምክር አገልግሎት ተጠቃሚው ሙሉ ስም--------------------------------

የባለሙያው ስም--------------------------------------------

የጉብኝት ቀን------------------------------ ፊርማ----------------------------

1. በጉብኝቱ ዕለት ውይይት የተደረገባቸው ሃሳቦች

1.1-----------------------------------------------------------------------------------------------

1.2-----------------------------------------------------------------------------------------------

1.3-----------------------------------------------------------------------------------------------

ሀ/ በኢንተርፕራይዙ ባለቤት ለችግሮቹ የተወሰዱ እርምጃዎች

ለ/ በባለሙያው የተሰጡ የድጋፍ ዓይነቶች

ሐ/ በቀጣይ ክትትል የሚያስፈልጋቸውና መፍትሔ ያላገኙ ችግሮች

2. በጉብኝቱ ወቅት የተነሱ አዳዲስ ሃሳቦች እና የተደረሰባቸው የትግበራ ስምምነቶች

ሀ/ ውይይቶችና የማጠቃለያ ሃሳቦች

ለ/ በምክር አገልግሎት ተጠቃሚው የሚተገበሩ ሥራዎች (አዳዲስ በተነሱ ሃሳቦች ዙሪያ)

ሐ/ አዳዲስ በተነሱ ችግሮች ዙሪያ ከባለሙያው የሚጠበቁ ተግባራት

ሪፖርቱ የተዘጋጀበት ቀን----------------------- -------------------------

የደንበኛው ሙሉ ስም-------------------------- -------------------------

ፊርማ-------------------------- ቀን---------------------

ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት የተላከበት ቀን-------------------------------------

በሚመለከታቸው አካላትና ክፍሎች ሪፖርቱ የተገመገመበት ቀን---------------------

ሪፖርቱን የገመገመው ባለሙያ፡-

ሙሉ ስም------------------------------------- ፊርማ---------------------------------ቀን------------

ከሪፖርቱ ጋር ተያይዘው ሊቀርቡ የሚገባቸው መረጃዎች

ሀ/ ባለሙያው በውይይቶችና ጉብኝት ወቅት ያገኛቸውንና የለያቸውን ዝርዝር ችግሮች

ለ/ የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡